# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላት ሱታፌ /ድርሻ/

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቸሩ አምላክ የሰው
ልጆችን ለማዳን ወዶና ፈቅዶ ባደረገው አምላካዊ የቸርነት ሥራ ውስጥ
ልዩ ድርሻ አላት:: በዚህም የነገረ ድኅነት ሱታፌዋ ምክንያት በኦርቶ
ዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ሥፍራ ተሰጥቶአታል::
ይህም ለዘመናት በቆየውና ከቀደሙት ቅዱሳን አበው ሊቃውንት በተ
ላለፈልን ቀጥተኛና አማናዊ ትምህርት መሠረት በግልጽ የምናየው
እውነታ ነው:: የቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊ አስተምህሮም በመጻሕ
ፍት አምላካውያት ላይ የተመሠረተና በዘወትር ሥርዓተ አምልኮዋም
የተገለጠ ሕያው ምሥጢር ነው::

በመሆኑም የእመቤታችን ሕይወት ከክርስትና እምነት
መጀመርና ከቤተ ክርስቲያን መመሥረት ጋር በእጅጉ የተዋሐደና የተ
ሰናሰለም ነው:: ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ልዑለ ባሕርይ
እግዚአብሔር ለድኅነተ ዓለም መሣሪያ አድርጎ ስለመረጣት የድኅነተ
ዓለምን ዜና ብሥራት ከሁሉ አስቀድማ የሰማች ናት:: በመሆኑም ይህ
አምላካዊ ጸጋ ከሌሎች ፍጡራን ሁሉ ልዩ ያደርጋታል:: ከዚህም ጋር
የእመቤታችን ሕይወት ከዕለተ ብሥራት ጀምሮ እስከ ዕለተ ዕርገት ድ
ረስ ከተደረገው አምላካዊ የማዳን ሥራ ጋር ፍጹም የተዋሐደ መሆኑ
በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ጉልህ ተሳትፎ በግልጥ ያሳያል::[30]

---

[30] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 232:: አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 155:: Wondemagegnehu and Motovou eds., *The Ethiopian Orthodox Church,* 106, David Daniel, trans., *Blessed Virgin Miriam* vol. II (New Delhi: Printed Aid, 1992), 133, Gambero, *Mary and the Fathers*



### 2.1 የዐሥራው መጻሕፍት ምስክርነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም
አስተምህሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ እመቤታችን
ቅድስት ድንግል ማርያም በዘመነ አበው በተለያየ ኅብረ አምሳል
መገለጧንና መታየቷን በስፋትና በጥልቀት ያስረዳል:: ከዚህም ጋር
በዘመነ ብሉይ የነበሩ ቅዱሳን ነቢያት በመንፈስ ትንቢት ተቃኝተው በተ
ለያየ ኅብረ ትንቢት ስለ እርሷ መናገራቸው በድኅነተ ዓለም አምላካዊ ዕ
ቅድ ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻ በምሥጢር ያሳያል:: በመሆኑም ስለ
እመቤታችን የተመሰለው ምሳሌና የተነገረው ትንቢት የሰው ልጆች ተ
ስፋ ድኅነት ፍጻሜ በሆነው በዘመነ ሐዲስ አማናዊ ሆኖ በመፈጸሙ
አዲስ ኪዳን ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ምክንያተ ድኅነት፣ መሠ
ረተ ሕይወት መሆኗን በግልጽ ያበሥራል::

ይህንን አስመልክቶ የብሕንሳው ሊቅ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ
እመቤታችንን ባመሰገነበት ቅዳሴው "ኦ ድንግል እምሳሌ ወትንቢት ዘነቢያት፤
ድንግል ሆይ የነቢያት ምሳሌና ትንቢት አንቺ ነሽ"[31] በማለት መስክሮ
ላታል:: ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም በወልደ
እግዚአብሔር ሰው መሆን (ምሥጢረ ሥጋዌ) አማካይነት የተፈጸመው
የድኅ ነተ ዓለም ሥራ እንደ እንግዳ ደራህ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ እንዲያው
በቅጽበት ወይም በድንገት የተደረገ ሳይሆን አስቀድሞ በተለያየ ኅብ
ረ አምሳልና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተገለጠ መሆኑን አስ
ረግጦ ተናግሮአል:: ለዚህም "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ

---

*of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought,* 46-47, 53-55. B. R. Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of Jesus* (Edinburgh: T & T Clark, 1995), 42-43. Michael O' Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary* (Wilmington, Delaware: Michael Glazier, Inc, 1982), 30-31.

[31] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 239:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 15:: H. F. Davis, "The Role of the Blessed Mother in the Economy of Salvation," *The Theology of Atonement: Readings in Soteriology,* ed. John R. Sheets (Englewood Cliffs, New Jersey: Prentice Hall, 1967), 45.

ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከሴትም ተወለደ:: እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ. 4÷4-5) በማለት መስክሮ አል:: በዚህም ሐዋርያዊ ቃል መሠረት ከላይ የገለጽነው የድኅነተ ዓለም ተስፋ በቅድስት ድንግል ማርያም እንደተፈጸመ ልብ ይሏል:: ዳግመኛም በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን የመጀመሪያውን ተአምር ባደረገበት በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት (ዮሐ. 2÷4)፤ እንዲሁም የድኅነተ ዓለም ሥራን በፈጸመበት በቀራንዮ መስቀል ላይ (ዮሐ. 19÷26) "አንቺ ሴት" ሲል መጥራቱ አስቀድሞ ለሰው ልጆች የሰጠው የድኅነት ተስፋ በእርሷ በኩል መፈጸሙን በምሥጢር ያጠይቃል::[35]

በቀዳሚት ሔዋንና [First Eve] በዳግሚት ሔዋን [Second Eve] በእመቤታችን መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር በየዘመኑ የተነሡ የተለያዩ አበው ሊቃውንትና መተርጉማን አምልተውና አስፍተው ገልጸዋል:: ይኸውም ቀዳሚት ሔዋን ለፈቃደ እግዚአብሔር ባለመታመኗና ባለመታዘዟ ምክንያት በመላው የሰው ዘር ላይ መርገምንና ሞትን አምጥታለች:: በአንጻሩ ደግሞ ዳግሚት ሔዋን የተባለችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለፈጣሪዋ ፈቃድ በመታመኗና በመታዘዟ ምክንያት በመርገምና በሞት ጥላ ሥር ወድቆ ለነበረው ዓለም በረከትንና ሕይወትን አስገኝታለች::[36] ይህንን አስመልክቶ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴው ሲናገር «በእንተ ሔዋን ተዐፅወ ኆኅተ ገነት፤ ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ፤ በቀዳሚት ሔዋን ምክንያት የገነት ደጃፍ ተዘጋብን፤ ዳግመኛም ስለ ዳግሚት ሔዋን ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን»[37] በማለት አስገንዝቦአል::

---

(35) Daniel, *Blessed Virgin Mariam,* 17-18. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers,* 25. *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው፣* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም.)፣ ገጽ 259::

(36) St. Jacob of Serug, *On the Mother of God.* trans. Mary Hansbury (Crestwood, New York.; St. Vladimir's Seminary Press, 1998), 82. Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept,* 47. Carol, *Mariology* vol. 2, 88-89.

(37) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 120:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣



ከዚህም ሌላ ሰፊና ጥልቅ በሆነው የነገረ ማርያም አስተምህሮው የዜና አበው ሊቃውንት «የነገረ ማርያም አባት» ["The Father of Mariology"] እያሉ የሚጠሩት ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ቅዱስ ሄሬኔዎስ [Irenaeus of Lyon] ከላይ የገለጥነውን ኃይለ ቃል መሠረት በማድረግ እመቤታችንን «የሔዋን ጠበቃ፣ አለኝታ» ብሎአታል:: በዜና አበው ክፍለ ትምህርት እንደሚታወቀው ይህ አባት የነበረበት ዘመን «የነገረ ማርያም ዘመነ ልደት» በመባል ይታወቃል::[38]

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለነገረ ድኅነት መሠረት መሆኗን በመግለጥ የተአምሯ መጽሐፍ «እግዝእትነ ማርያም ነበረት እምቅድመ ዓለም በኅሊና አምላክ»[39] ይላል:: ከዚህም ኃይለ ቃል ድኅነተ ዓለም የተፈጸመበትና የተከናወነበት የምሥጢረ ሥጋዌ ጉዞ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ የፈቀደውና ያሰበው የቸርነቱና የመግቦቱ ሥራ መሆኑን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን:: ከዚህም ጋር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «ወበእንተ ዝንቱ አስተርአየ ወልደ እግዚአብሔር ከመ ይስዐር ግብሮ ለጋኔን፤ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1ኛ ዮሐ. 3÷8) ሲል እንደመሰከረው ጥንተ ጠላታ ችን የሆነው ዲያብሎስ በሥጋ ከይሲ ተሠውሮ አዳምንና ሔዋንን እንዳሳተ ሁሉ (ዘፍ. 3÷1-14)፤ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ ብእሲ ተሠውሮ ወደ ቀደመው ጸጋና ክብር መልሶአቸዋል::

---

ሰአሊ ለነ ቅድስት፣ ገጽ 42-45:: Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God,* 43, 59. Jacob of Serug, *On the Mother of God,* 39.

(38) Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept,* 48. Carol, *Mariology* vol. 2, 89. Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary,* 189.

(39) *ተአምረ ማርያም፣* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም.)፣ ገጽ 3-4:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 379:: ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መሪ ጌታ)፣ «እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ»፤ ገጽ 8:: Kallistos Ware, *The Orthodox Way,* Revised Edition (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1996), 71. Henry Bettenson, ed. & trans. *The Early Christian Fathers* (Oxford: Oxford University Press, 1956), 291, 293. J. N. D. Kelly, *Early Christian Doctrines* (New York: Prince Press, 2003), 346-347. Ware, *The Orthodox Church,* 255.

ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» (ዕብ. 1÷1-2) የሚለው ኃይለ ቃል በቂ ማስረጃና ምስክር ነው:: ይሁን እንጂ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የተመሰለውን ኅብረ አምሳልና የተነገረውን ትንቢት በሙሉ በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ በዝርዝር ለማቅረብና ለማብራራት አይቻልም:: ስለሆነም መጠነ ሰፊ ከሆኑት ኅብረ አምሳልና ኅብረ ትንቢት መካከል የተወሰኑትንና ከነገረ ድኅነት ጋር የተያያዘ ሰፊና ጥልቅ ምሥጢር ያላቸውን ብቻ ለማየት ተሞክሯል:: እነዚህም:- ዳግሚት (አዲሲቷ) ሔዋን፣ ሐመረ ኖኅ (የኖኅ መርከብ)፣ ዕፀ ሳቤቅ እና ሰዋስወ ያዕቆብ (የያዕቆብ መሰላል) ናቸው:: ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው እነዚህ ምሳሌዎችና ትንቢቶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያም አስተምህሮ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ግንኙነትና ምሥጢራዊ ትሥሥር በግልጥ ያስረዳሉ::

### 2.1.1. ዳግሚት ሔዋን (አዲሲቷ ሔዋን)

ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር «በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትነክሳለህ::» (ዘፍ. 3÷15) ሲል የተናገረው ይህ ተስፋ ትንቢት መፍቀሬ ሰብእ የሆነው አምላክ ለሰው ልጆች ያለውን አምላካዊ የአድኅኖት ዕቅድና በጎ ፈቃድ የሚገልጥ መሪ ቃለ ተስፋ ነው:: በመሆኑም ይህ አምላካዊ ተስፋ ትንቢት በምክረ ከይሲ ተታለው፣ በኃጢአት ተሰናክለው፣ በመንጸፈ ደይን ወድቀው፣ በእግረ አጋንንት ይጠቀጠቁ ለነበሩት ለአባታችን አዳምና ለእናታችን ሔዋን እንዲሁም ለልጆቻቸው ሁሉ የተሰጠ የመጀመሪያ አምላካዊ የድኅነት ተስፋ ነው::[32] ስለሆነም መጽሐፍ «ተፈጸመ ተስፋ አበው በማርያም ድንግል፤ ወበቀራንዮ ተተክለ

[32] Judith A. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers* (Liguoiri, Missouri: Liguori Publications, 1999), 24. Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept,* Book IV, 52. Davis, "The Role of the Blessed Mother in the Economy of Salvation," 45.



ዐድኅኒት ዐስቀል፤ የቅዱሳን አበው ተስፋ ድኅነት በቅድስት ድንግል ማርያም ተፈጸመ፤ የድኅነተ ዓለም ሥራ የተፈጸመበት መድኃኒት መስቀልም በቀራንዮ ተተከለ»[33] እንዳለው ወላዲተ አምላክ የዚህ ቃለ ትንቢት ፍጻሜ መሠረት መሆኗን ይመለከቷል::

ከላይ የጠቀስነው የምሥጢረ ድኅነተ ዓለም ቃለ ትንቢት ለጊዜው በቀዳሚት ሔዋንና በጥንተ ጠላታችን በዲያብሎስ መካከል ያለውን ጸብና ክርክር የሚያሳይ ሲሆን፤ ፍጻሜ ምሥጢሩ ግን በዳግሚት ሔዋን (አዲሲቷ ሔዋን) በድንግል ማርያምና ምክንያተ ስሕተት በሆነው በሰይጣን መካከል የሚኖረውን ጠላትነት የሚገልጥ ነው:: (ራእ. 12÷1-17) ከዚህም ሌላ የሴቲቱ (የድንግል ማርያም) ዘር በሆነው በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በሠራዊተ አጋንንት መካከል የሚኖረውን ጠላትነትም ያስረዳል:: ይህም ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ» (መዝ. 73÷14) ባለው መሠረት የድንግል ማርያም ልጅ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ጥንተ ጠላታችን የሆነውን የዲያብሎስን ራስ በመስቀል ላይ ቀጥቅጦአል:: በአንጻሩ ደግሞ «እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ» (መዝ. 21÷16) ተብሎ እንደተጻፈ ጠላት ዲያብሎስ በአይሁድ ልቡና አድሮ የመድኃኒታችንን ቅዱሳት እግሮች በቀኖት አስቸንክሮአል:: (ዮሐ. 19÷23፣ 34፤ 20÷25)[34]

ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን ድንቅ ምሥጢረ ድኅነት አስመልክቶ ሲናገር «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ

[33] አባ ስብሐት ለአብ፣ «ነግሥ»፤ *መጽሐፈ ሰዓታት ወመዝገበ ጸሎት፣* (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 532::

[34] *መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣* (አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1982 ዓ.ም.)፣ ገጽ 372-373:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ 1988 ዓ.ም.) ገጽ 378:: Kevin McNamara ed., *Mother of the Redeemer: Aspects of Doctrine and Devotion* (New York: Sheed and Ward, Inc., 1960), 153-155. Dom Ralph Russell, "The Blessed Virgin Mary in the Bible: The Scriptural Basis of Ecumenical Dialogue," Alberic Stacpoole, ed., *Mary's Place in Chrisitan Dialogue* (Wilton, Connecticut: Morehouse-Barlow Co., Inc., 1983), 46. Jean Galot, *Mary in the Gospel* (Westminster, Maryland: The Newman Press, 1965), 199-200.

ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከሴትም ተወለደ፡፡ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ. 4÷4-5) በማለት መስክሮ አል፡፡ በዚህም ሐዋርያዊ ቃል መሠረት ከላይ የገለጽነው የድኅነተ ዓለም ተስፋ በቅድስት ድንግል ማርያም እንደተፈጸመ ልብ ይሏል፡፡ ዳግመኛም በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን የመጀመሪያውን ተአምር ባደረገበት በገሊላ ቃና ሠርግ ቤት (ዮሐ. 2÷4)፤ እንዲሁም የድኅነተ ዓለም ሥራን በፈጸመበት በቀራንዮ መስቀል ላይ (ዮሐ. 19÷26) "አንቺ ሴት" ሲል መጥራቱ አስቀድሞ ለሰው ልጆች የሰጠው የድኅነት ተስፋ በእርሷ በኩል መፈጸሙን በምሥጢር ያጠይቃል፡፡(35)

በቀዳሚት ሔዋንና [First Eve] በዳግሚት ሔዋን [Second Eve] በእመቤታችን መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር በየዘመኑ የተነሡ የተለያዩ አበው ሊቃውንትና መተርጉማን አምልተውና አስፍተው ገልጸዋል፡፡ ይኸውም ቀዳሚት ሔዋን ለፈቃደ እግዚአብሔር ባለመታመኗና ባለመታዘዟ ምክንያት በመላው የሰው ዘር ላይ መርገምንና ሞትን አምጥታለች፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ዳግሚት ሔዋን የተባለችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለፈጣሪዋ ፈቃድ በመታመኗና በመታዘዟ ምክንያት በመርገምና በሞት ጥላ ሥር ወድቆ ለነበረው ዓለም በረከትንና ሕይወትን አስገኝታለች፡፡(36) ይህንን አስመልክቶ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴው ሲናገር "በእንተ ሔዋን ተዐፅወ ኆኅተ ገነት፤ ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ፤ በቀዳሚት ሔዋን ምክንያት የገነት ደጃፍ ተዘጋብን፤ ዳግመኛም ስለ ዳግሚት ሔዋን ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን"(37) በማለት አስገንዝቦአል፡፡

(35) Daniel, *Blessed Virgin Mariam*, 17-18. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 25. *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው፣* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም.)፣ ገጽ 259፡፡

(36) St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*. trans. Mary Hansbury (Crestwood, New York.; St. Vladimir's Seminary Press, 1998), 82. Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept*, 47. Carol, *Mariology* vol. 2, 88-89.

(37) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 120፡፡ ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣



ከዚህም ሌላ ሰፊና ጥልቅ በሆነው የነገረ ማርያም አስተምህሮው የዜና አበው ሊቃውንት "የነገረ ማርያም አባት" ["The Father of Mariology"] እያሉ የሚጠሩት ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ቅዱስ ሄሬኔዎስ [Irenaeus of Lyon] ከላይ የገለጥነውን ኃይለ ቃል መሠረት በማድረግ እመቤታችንን "የሔዋን ጠበቃ፣ አለኝታ" ብሎአታል፡፡ በዜና አበው ክፍለ ትምህርት እንደሚታወቀው ይህ አባት የነበረበት ዘመን "የነገረ ማርያም ዘመነ ልደት" በመባል ይታወቃል፡፡(38)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለነገረ ድኅነት መሠረት መሆኗን በመግለጥ የተአምሯ መጽሐፍ "እግዝእትነ ማርያም ነበረት እምቅድመ ዓለም በኅሊና አምላክ"(39) ይላል፡፡ ከዚህም ኃይለ ቃል ድኅነተ ዓለም የተፈጸመበትና የተከናወነበት የምሥጢረ ሥጋዌ ጉዞ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ የፈቀደውና ያሰበው የቸርነቱና የመግቦቱ ሥራ መሆኑን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን፡፡ ከዚህም ጋር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ "ወበእንተ ዝንቱ አስተርአየ ወልደ እግዚአብሔር ከመ ይስዐር ግብሮ ለጋኔን፤ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ" (1ኛ ዮሐ. 3÷8) ሲል እንደመሰከረው ጥንተ ጠላታ ችን የሆነው ዲያብሎስ በሥጋ ከይሲ ተሠውሮ አዳምንና ሔዋንን እንዳሳተ ሁሉ (ዘፍ. 3÷1-14)፤ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ ብእሲ ተሠውሮ ወደ ቀደመው ጸጋና ክብር መልሶአቸዋል፡፡

*ሰአሊ ለነ ቅድስት፣* ገጽ 42-45፡፡ Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 43, 59. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 39.

(38) Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept*, 48. Carol, *Mariology* vol. 2, 89. Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary*, 189.

(39) *ተአምረ ማርያም፣* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም.)፣ ገጽ 3-4፡፡ ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 379፡፡ ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መሪ ጌታ)፣ "እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ"፤ ገጽ 8፡፡ Kallistos Ware, *The Orthodox Way*, Revised Edition (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1996), 71. Henry Bettenson, ed. & trans. *The Early Christian Fathers* (Oxford: Oxford University Press, 1956), 291, 293. J. N. D. Kelly, *Early Christian Doctrines* (New York: Prince Press, 2003), 346-347. Ware, *The Orthodox Church*, 255.

ይህንንም ምሥጢር ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አሞንዮስና አውሳብዮስ በመቅድመ ወንጌል ሲገልጡ "ወበከመ ተኃብአ ሰይጣን በጉሕሉቱ ውስተ ሥጋ ከይሲ፤ ከማሁ ኮነ ድኅነትነ በተሠውሮቱ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ፤ ሰይጣን በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ አዳምን እንዳሳተው፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ ብእሲ ተሰውሮ መጥቶ ዓለምን አዳነ"[40] በማለት ተናግረዋል:: በዚህም ትርጓሜ ምሥጢር መሠረት የሰው ልጅ በምክረ ከይሲ ተታሎ ሕገ እግዚአብሔርን አፈረሰ፤ በኃጢአቱም ምክንያት ከፈጣሪው አንድነት ተለየ ሲባል በአካለ ከይሲ ተደልሎ፣ በልሳነ ከይሲ ተታሎ መሳቱን መናገር ነው:: ስለሆነም ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ አካለ ከይሲን መሰወሪያ፣ ልሳነ ከይሲን መናገሪያ አድርጎ በማሳቱ በማጎደሩ ኃዳሪውን መናገር ነው እንጂ ለሰው ልጅ ስሕተት ምንጬና መሠረቱ ራሱ ዲያብሎስ መሆኑን መረዳት ያሻል::

ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳል መገለጧና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት መነገሯም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻ በጥልቀት ያስረዳል:: በዚህም መሠረት የነገረ ማርያም ትምህርት ከነገረ ድኅነት ትምህርት ጋር የተያያዘ ጥልቅ ምሥጢር እንዳለው ልብ ይሏል:: የመጋቤ ሐዲስ የቅዱስ ገብርኤል ዜና ብሥራትና የእመቤታችን ተአምኖና ተአዛዚተ እግዚአብሔር መሆን የመሲሕ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣትና የአዲስ ኪዳንን መጀመር ያበሥራል:: በአጠቃላይ ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢር በተመለከተ አራቱ ወንጌላውያን ይልቁንም ደግሞ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የእመቤታችንን ሁለንተናዊ ሕይወት በመግለጥ በልዑል እግዚአብሔር ፊት ያላትን ክብርና የባለሟልነት ሞገስ እንዲሁም ከመልአከ ብሥራቷ ከቅዱስ ገብርኤል ጋር ያደረገችውን ቃለ ምልልስ በሰፊው ተናግሮላታል::[41]

[40] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.)፣ ገጽ 28::

[41] George H. Tavard, The Thousand Faces of the Virgin Mary (Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1996), 6-16. አንዱዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ "እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል"፣ ፍሬ ተዋሕዶ ዘእምናዝሬት፣ የካቲት 20/1997 ዓ.ም. ገጽ 1፣ 7::



በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ አምላካዊ የድኅነተ ዓለም ጉዞ በማኅፀነ ድንግል እንዲጀመር ምክንያትና መሠረት የሆነው የመልአከ ሰላም የቅዱስ ገብርኤል ዜና ብሥራት አስቀድሞ የሰው ልጆች በኃጢአት የወደቁበትን፣ መርገምና ሞት ወደ ዓለም የገባበትን የመልአከ ጽልመት የዲያብሎስን ተንኮል የሻረና ክፉ ምክሩንም ያፈረሰ የበረከትና የሕይወት መንገድ ነው:: በመሆኑም በእመቤታችን በድንግል ማርያም አማካይነት የተፈጸመው የሥጋዌ ምሥጢር መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ቸሩ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ጥልቅ ፍቅር የገለጠበት ታላቅ የድኅነት ምሥጢር ነው:: በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው የመጀመሪያይቱ ሔዋን በምክረ ከይሲ ተታልላ የጠላት ዲያብሎስን ክፉ ምክር ሰምታ በመቀበሏ ምክንያት ለሰው ልጆች ድቀት (ውድቀት) እንዲሁም የሞት ፍርድ ምክንያት ሆናለች:: (ዘፍ. 3፥4-6)

በአንጻሩ ደግሞ ዳግሚት ሔዋን የተባለችው ቅድስት ድንግል እመቤታችን በልዑል እግዚአብሔር ፊት በባለሟልነት የሚቆመውን የመልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤልን ቃለ ብሥራት ሰምታ "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ" ብላ በእምነት በመቀበሏ ምክንያተ ድኂን ሆነችን::[42] ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጐም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በማኅፀኗ አደረ:: በመሆኑም ቀዳሚት ሔዋንን ምክንያተ ስሕተት፣ ምክንያተ ሞት በመሆኗ ሲወቅሳትና ሲከሳት የነበረው የሰው ዘር በሙሉ ምክንያተ ድኅነት፣ ምክንያተ በረከት ወሕይወት የሆነች ዳግሚት ሔዋን እመቤታችንን "ብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገረኪ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከው፣ ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽ ቃል

[42] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ "መጽሐፈ ምሥጢር" ["The Book of Mystery"] *CSCO* vol. 515, *Scriptores Aethiopici*, 97. Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept*, Book. IV, 47-49. John Baggely, *Doors of Perception: Icons and Their Spiritual Significance* (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1995), 128, 144. Kelly, *Early Christian Doctrines*, 347, 352. ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ ለአሊ ለነ ቅድስት፣ ገጽ 12::

እንዲፈጸም የምታምኚ አንቺ በእውነት ብፅዕት ነሽ፣ ንዕድ፣ ክብርት ነሽ» (ሉቃ.1÷28-38) እያለ የሚያመሰግናት ሆኗል::


ከላይ እንደገለጥነው ወላዲተ አምላክ የቅዱስ ገብርኤልን ዜና ብሥራት ሰምታ በማመኗ ምክንያት መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ስለመጣ ብሥራተ መልአክ የብሉይ ኪዳን አምሳልና ትንቢት ፍጻሜ ወይም መደምደሚያ ሆነ:: ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢር አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም መጽሐፍ ሲናገር «ወቅዱስ ገብርኤል በቃለ ብሥራቱ ኀተመ ትንቢቶሙ ለነቢያት:: ገብርኤል ውእቱ ዘአፈለፈለ ለቲ ፍሥሐ ለኵሉ ዓለም ወአብጠለ እምአልባበ ሰብእ ኵሉ ለቲ ኀዘን መሪር ዘየአኪ እምሕምዘ አፍዖት ዘጸቀትል»(43) ይላል:: ይህም ማለት «ቅዱስ ገብርኤል ብምሥራቹ ቃል የቅዱሳን ነቢያትን ትንቢት አተመ፣ አጸና፣ ፈጸመ፣ ዘጋ፣ አረጋገጠ:: ለዓለም ሁሉ የደስታ መጠጥንና ምንጭን ያፈለቀ፣ ያስገኘ፣ ያመነጨ ገዳይ ከሆነ የእባብ (የአውሬ) መርዝም የሚከፋ መራራ የኃዘን ውኃን (መጠጥን፣ ምንጭን) ከሰው ሁሉ ልቡና ያስወገደ ያራቀ ይህ ቅዱስ ገብርኤል ነው» ማለት ነው::

በዚህም መሠረት ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የጻፈው የነገ ረ ብሥራት ምሥጢር ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ሥጋዌ ትምህርት ምንጭ ለሆነው የነገረ ማርያም ትምህርት ዐቢይ መሠረት ጥሏል:: ከዚህ በተጨማሪም ብሥራተ መልአክ የሰው ልጆችን አስከፊ የኃጢአትና የመርገም ታሪክ የቀየረ ታላቅ ክስተት በመሆኑ(44) ለቤተ ክርስቲያናችን ጥልቅ የነገረ ድኅነት አስተምህሮም በቂ ማስረጃና ምስክር ነው::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለመልአኩ ዜና ብሥራት በሰጠችው ቃለ ተአምኖ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከጥንት

(43) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia* vol. 24, 23.
(44) Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 43.





ሥዕል 1:- መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን እንዳበሠራት

«ደስ ያለህ ባለምሥራች ገብርኤል ሆይ ላንተ የተሰጠህ ክብር ፍጹም ነው:: ወደ እኛ የመጣ የጌታን ልደት ለእመቤታችን ነገርካት::»

(ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 100-101)

«ግርምት ድንግል እመቤታችን ሆይ ክብርሽን ገናንነትሽን ዕፁብ ዕፁብ እያልን እናመሰግናለን:: እንደ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ምስጋና እናቀርብልሻለን:: የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርያችን ድኅነት ሆኗልና::»

(ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 170)

ያሰበውና የፈቀደው የድኅነተ ዓለም ሥራ እንዲፈጸምና አማናዊ እንዲሆን አድርጋለች:: ይህም ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ታላቅ ሱታፌ በጉልህ ያሳያል:: ይህንን ምሥጢር በተመለከተ ኢትዮጵያዊው ሊቅ በድርሰቱ «ዘበቃሉ ጕሕሉቱ ለሰይጣን መልአከ ስሕተት ተሰፍሐ ግባ ጽልመት ውስተ ኵሉ ዓለም፤ ወበቃለ ብሥራቱ ለገብርኤል መልአከ ጽድቅ ተሰፍሐ ብርሃነ ሕይወት ውስተ ኵሉ ዓለም፤ የስሕተት አለቃ በሆነው በሰይጣን የክፋትና የጥፋት ቃል ምክንያት የጨለማ መጋረጃ በዓለም ሁሉ እንደተዘረጋ፤ የእውነት መልአክ በሆነው በቅዱስ ገብርኤል የምሥራች ቃል ደግሞ የሕይወት ብርሃን በዓለም ሁሉ ተዘረጋ»[45] በማለት መስክሮአል::

ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም እመቤታችን በነገ ረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ልዩ ሥፍራ ሲናገር «በእንተ ተሠግዎቱ ለወልደ አምላክ እምኔኪ ቅሩባነ ኮነ እምድር ውስተ አርያም፤ ብኪ ወበስመ ወልድኪ»[46] ብሏል:: የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋሽ ሥጋ፣ ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ ካንቺ ሰው በመሆኑ ከምድር ወደ ሰማይ፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከመርገም ወደ በረከት፣ ከኃሣር ወደ ክብር፣ ከሲኦል ወደ ገነት ተሸጋገርንብሽ ማለት ነው::

ከላይ የተመለከትነውን በቀዳሚት ሔዋንና በዳግሚት ሔዋን መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር [Typology] አስመልክቶ "ኢትዮ ጵያዊው ቄርሎስ" በመባል የሚታወቀው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሲገልጽ «ለእመ ኃሠሥካ ለሔዋን ትረክባ በህየ እንዘ ትትፌሣሕ በወለታ ዘአምጽአት ላቲ ፈውሰ ለቊስሊሃ፤ ለእመ ኃሠሥኮ ለአዳም ትረክቦ በህየ እንዘ ይትፌሣሕ ወይገብር በዓለ ምስለ ዳግማዊ አዳም»[47] በማለት በንጽጽሩ ውስጥ ያለውን

[45] Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia* vol. 24, 24. Davis, "The Role of the Blessed Mother in the Economy of Salivation," 45-46.

[46] ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 402::

[47] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla], *መጽሐፈ ምሥጢር፣ ["Il Libro Del Mistero"]*፣ ገጽ 71:: See also Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 97. Brock, *Bride of Light*, 111. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 230::



ጥልቅና ረቂቅ ምሥጢረ ድኅነት አስተምሯል:: እንደ ሊቁ አገላለጽ ዳግሚት ሔዋን የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፍሬ ሕይወት ወመድኃኒት የሆነው ጌታ የተገኘባት አማናዊት ዕፀ ሕይወት በመሆኗ የዕፀ በለሰን ፍሬ በልታ ሞትን ላመጣችብን ለቀዳሚት ሔዋን ካሣ ናት:: ምክንያቱም ከዳግሚት ሔዋን ከድንግል ማርያም የተወለ ደው የማኅፀኗ ፍሬ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ሥጋ፤ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ፤ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን የሚያድል ሕይወተ ሥጋን ሕይወተ ነፍስን የሚሰጥ፣ ቀዳሴ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ የሆነ ቡሩክ አምላክ ነውና::[48]

## 2.1.2 ሐመረ ኖኅ (የኖኅ መርከብ)

በቅዱስ መጽሐፍ ከተመዘገቡት አሳዛኝና አስከፊ ታሪኮች መካከል አንዱ የማየ አይኅ (የጥፋት ውኃ) ታሪክ ነው:: በጻድቁ ኖኅ ዘመን የነበሩት ሰብአ ትካት ከሕገ እግዚአብሔር ወጥተው በማይገባ የኃጢአትና የበደል ሕይወት ውስጥ በመገኘታቸው የእግዚአብሔር ቁጣ እንደነደደባቸው እንመለከታለን:: ይሁን እንጂ ብእሴ እግዚአብሔር የሆነው ጻድቁ ኖኅ ከዚህ አስፈሪ ቁጣና አምላካዊ ቅጣት እንዲድን የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለነበረ ተግቶና ነቅቶ በሠራት ባለ ሦስት ክፍል መርከብ አማካይነት ከጥፋት ውኃ ድኖአል:: (ዘፍ. 6÷14-8÷19፤ ዕብ. 11÷7) የአዲስ ኪዳን ሊቃውንት ለድኅነተ ዓለም ምክንያት የሆነችው ቤ ዛዊተ ዓለም ቅድስት ድንግል ማርያምን በሐመረ ኖኅ ይመስሏታል:: ይህንን አስመልክቶ የብሕንሳው ሊቅ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እመቤ ታችንን ባመሰገነበት ቅዳሴው «ታቦት አንተ ኖኅ በዘባቲ ድኅነ እምአይኅ፤ ኖኅ ከማየ ሥራዌ፣ ከማየ ድምሳሴ (ከጥፋት ውኃ) የዳነባት መርከብ አንች ነሽ»[49] በማለት መስክሮላታል::

[48] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 328-329::

[49] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 79:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 384:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 180:: ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መሪጌታ)፣ "እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ"፣ *ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ*፣ ሰኔ/

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንዳመሰጠሩት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ሊመጣ ካለው አምላካዊ መቅሰፍት ሸሽተው፣ መርከቢቱን ጥግ አድርገው በውስጧ የተሸሸጉትን ነፍሳት በቸርነቱ ጠብቆና በጽላሎተ ረድኤቱም ከልሎ አድኗቸዋል:: ስለሆነም ሰብአ ትካትን ያጠፋውና የደመሰሰው ማየ አይኅ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት በዓለሙ ሁሉ ሰፍኖ የነበረውና የሰው ልጆችን በፍዳና በመርገም ይዞ የሚኖረው የምልአተ ኃጢአት ምሳሌ ነው:: አማናዊቷ ሐመረ ኖኅ እመቤታችንም ከማየ ኃጢአትና ከጥፋት ማዕበል የዳንባት የሕይወት መርከብ፣ የዕረፍት ወደብ በመሆኗ ይህ ምሳሌዋ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይገልጣል::[50]

ከላይ እንደገለጥነው ሐመረ ኖኅ የእመቤታችን ምሳሌ ስትሆን፣ ጻድቁ ኖኅ ደግሞ ፍጥረቱን ሁሉ በእጁ የያዘ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው:: ማየ አይኅ የሰው ልጅን በሞት ፍዳ አስይዞ የነበረው የምልዓተ ኃጢአት ምሳሌ ነው:: ከዚህም ጋር የኖኅ ወደ መርከቢቱ መግባት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማኅፀነ ድንግል የማደሩ ምሳሌ ነው:: ብእሴ እግዚአብሔር ኖኅ ከመርከቢቱ መውጣቱ ደግሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአማናዊቷ ሐመረ ኖኅ ከድንግል ማርያም መወለዱን ያመለክታል::

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ሐመረ ኖኅ ባለ ሦስት ክፍል መሆኗ እመቤታችን በሦስት ወገን ንጽሕት እንደሆነች ማለትም በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና ያጌጠችና የከበረች መሆኗን ያጠይቃል:: አንድም በሐልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር ንጽሕት መሆኗን ያሳያል:: አንድም በሦስቱ ድንግልናዋ ማለትም:- ቅድመ ጸኒስ (ከመጽነሷ በፊት)፣ ጊዜ ጸኒስ (በጸነሰች ጊዜ)፣ ድኅረ ጸኒስ (ከጸነሰችም በኋላ)፤ ዳግመኛም ቅድመ ወሊድ

ሐምሌ 1991 ዓ.ም.፣ ገጽ 11::

(50) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia*, vol. 24, 4. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 39, 63. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 216:: *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 36፣ 74፣ 93::



(ከመውለዷ በፊት)፣ ጊዜ ወሊድ (በወለደች ጊዜ)፣ ድኅረ ወሊድ (ከወለደችም በኋላ) ዘላለማዊት ድንግል መሆኗን ያሳያል::

ሐመረ ኖኅ ምድርን መልቶ ከነበረው ከማየ አይኅ በላይ ሆና መታየቷም አማናዊቷ ሐመረ ኖኅ ቅድስት ድንግል ማርያም ማየ ኃጢአት ያልደረሰባትና ያልነካት፤ መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ ያላገኛትና ያልወደቀባት ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና መሆኗን ያስረዳል:: ሌላው ደስ የሚያሰኘው ምሥጢር ደግሞ ምድር ሐመረ ኖኅን ጥግ አድርገው ከማየ ሥራዌ፣ ከማየ ድምሳሴ በዳኑ ነፍሳት እንደተመሳች ሁሉ፤ ገነት መንግሥተ ሰማያትም በአማናዊቷ ሐመረ ድኅነት በእመቤታችን አማካይነት ከማየ ኃጢአት ድነው በመንፈስ ልደት በከበሩ ምእመናን መመላቷ ነው::[51]

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያም ትምህርት እመቤታችን ከማየ አይኅ የመዳን ምሥጢር ጋር በተያያዘ «እውነተኛ ሰላማዊት የኖኅ ርግብ» ትባላለች:: በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው በማየ አይኅ ጊዜ ኖኅ የውኃውን መጉደል ለመረዳት ይችል ዘንድ ርግብን ልኳል:: ይህች ርግብም ተልእኮዋን ፈጽማ ወደ ኖኅ ስትመለስ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ቸርነት ለፍጥረት ሁሉ የሚያበስር መልካም የምሥራች ዜና ይዛ መጥታለች:: ለዚህ የሰላም አዋጅ ምልክት ይሆን ዘንድ የለመለመ የወይራ ዝንጣፊ በአፏ ይዛ «ሐጸ ማየ አይኅ፣ ነትገ ማየ አይኅ፤ የጥፋት ውኃ ጎደለ፣ ደረቀ» የሚለውን የይቅርታ መልእክት አስተላልፋለች:: (ዘፍ. 8÷8-12)

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አማናዊት ርግብ መባሏም ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት በማየ ኃጢአት ተውጦና ሰጥሞ

(51) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 232:: ደጀኔ ሺፈራው (ዲያቆን) እና እሸቱ ታደሰ (ዲያቆን)፣ *ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ*፣ (አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም.)፣ ገጽ 26-27:: ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መሪጌታ)፣ «እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ»፣ ገጽ 11:: Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 38.

ለነበረው መላው የሰው ዘር የድኅነተ ዓለምን ዜና ብሥራት ዕፀ ሕይወት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በማኅፀኗ ተሸክማ "ሐጸ ማየ ኃጢአት፣ ነትገ ማየ ኃጢአት፤ የኃጢአት ውኃ ጎደለ፣ የበደል ውኃ ደረቀ" ስትል ያበሰረች ሰላማዊት ርግብ ስለሆነች ነው:: ሊቁ "እመ እተውኪ ውስተ ታቦት ምስለ ቍጽለ ዘይት ሐመልሚል፤ ከመ አብሠርኪዮ ለኖኅ ትእምርተ ጊዜሁ ለሣህል፤ አብሥርኒ ጽድቀ በጸዊረ ጽጌ ዕዱል፤ ማርያም ርግበ ቍስቋም ዘአክናፍኪ መስቀል"[52] እንዳለ:: በዚህም መሠረት ከሁሉ አስቀድማ የድኅነተ ዓለምን ዜና ብሥራት ከመልአኩ ከቅዱስ ገብርኤል አንደበት የሰማችና ይህን ቃለ ፍሥሐ በመንጸፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቅ፣ በዚህም ምክንያት ለዘመናት አዝኖና ተክዞ ይኖር ለነበረው መላው የሰው' ዘር ያሰማችና ያበሰረች እርሷ ብቻ ስለሆነች እውነተኛ ሰላማዊት ርግብ ትባላለች::

ስለዚህም መጻሕፍት አምላካውያት በመተባበር "ተፈሥሒ ኦ ሙኃዘ ፍሥሐ፣ የተድላና የደስታ መፍሰሻ ሆይ ደስ ይበልሽ"[53] እያሉ ያመሰግኗታል:: ሌላው ደግሞ እመቤታችን በኃጢአት ወድቆ የነበረው የሰው ልጅ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከመርገም ወደ በረከት፣ እንዲሁም ከግራ ቁመት ወደ ቀኝ ቁመት የተሸጋገረባት የሕይወት ድልድይ በመሆኗ እኛም ከዘላለም ጥፋት የምንሸሽግባት ሐመረ መድኃኒት (የድኅነት መርከብ) ናት::[54]

(52) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 230፣ 251:: Brock, *Bride of Light*, 140. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, vol.1 trans. Wedad Abbas (Cairo: Dar El Tebaa El Kawmia Press, 1996), 158. አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ ["Abba Giyorgis Di Sagla"], *ዕንዚራ ስብሐት ["The Lyre of Glory"]*, ed. M. V. D. Oudenrija, *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium*, vol. 208, *Scriptores Aethiopici*, t. 39-40 (text) (Louvain: Secretariat du CorpusSCO, 1960)፣ 4፣ 8፣ 50:: አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ *መጽሐፈ ሰዓታት ወመዝገበ ጸሎት*፣ (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 616::

(53) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 56:: ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 411:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 29:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia*, vol. 24, 27.

(54) አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 636:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia*, vol. 24, 200.



## 2.1.3 ሰዋስወ ያዕቆብ (ያዕቆብ መሰላል)

ኦርቶዶክሳውያን ሲቃውንት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለአካላዊ ቃል ርደት፣ ለሥጋ ዕርገት ምክንያት በመሆኗ "ወሰዋስዊሁ ለያዕቆብ፤[55] ያዕቆብ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ፣ በላይዋ ዙፋን ተነጽፎባት፣ በዚያ ላይ ንጉሥ ተቀምጦባት፣ መላእክት ሲወጡ ባት ሲወርዱባት በፍኖተ ሎዛ ያየት የወርቅ መላል አንቺ ነሽ" እያሉ ያመሰግኗታል:: መጽሐፍ ቅዱስ ያዕቆብ በምድረ ሎዛ ስላየው አስደናቂ ሕልም በግልጽ ያስረዳናል:: ቅዱስ ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ድንጋይ ተንተ ርሶ እንደተኛ ሌሊት ግሩም የሆነ ራእይን ተመለከተ:: ይኸውም የወርቅ መሰላል ተተክላ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ፣ በመሰላሏ ላይም ቅዱሳን መላእክት ሲወጡባትና ሲወርዱባት፣ በመሰላሏ ጫፍ ላይ ደግሞ ታላቅ ዙፋን ተዘርግቶባት ኃያል ንጉሥም ተቀምጦባት አየ:: (ዘፍ. 28÷10-16)

የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን ይህ አስደናቂ ሕልም ከነገ ረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ግንኙነት በሚገባ አምልተውና አስፍተ ው አስተምረዋል:: መተርጉማኑ እንደገለጹት መሰላሏ የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያም ምሳሌ ስትሆን፤ ቅዱስ ያዕቆብ ተንተርሶት የነበረው ድንጋይ ደግሞ የትንቢተ ነቢያት ምሳሌ ነው:: ምክንያቱም እመቤታችን በትንቢተ ነቢያት መሠረት ጸንታ ተገኝታለችና ነው:: ምንም እንኳን ብሉይ ኪዳን ቅድስት ድንግል ማርያምን በስሟ ጠርቶ ባይገልጻትም እመቤታችን በተለያየ ኅብረ አምሳልና በብዙ ዓይነት ኅብ ረ ትንቢት መገለጧ ግን የታወቀና የታመነም ነው:: ሰማያውያን የሆኑት ቅዱሳን መላእክት በመሰላሏ አማካይነት ወደ ላይ መውጣታቸውና ወደ ታች መውረዳቸው በአማናዊቷ ሰዋስው (የሕይወት መሰላል) በወላዲተ አምላክ ምክንያት ሰማይና ምድር መታ

(55) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 90-91:: አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ [Abba Giyorgis Di Sagla], *ዕንዚራ ስብሐት ["The Lyre of Glory"]*, vol. 208, 2.

ረቃቸውንና አንድ መሆናቸውንም ያጠይቃል::

የሰማይና የምድር ዕርቅ ሲባልም ትርጓሜ ምሥጢሩ የእግዚ አብሔርና የሰው መታረቅ፣ የቅዱሳን መላእክትና የሰዎች አንድነትና ኅብረት ማለት ነው:: በመሰላሏ ጫፍ የተዘረጋው ዙፋን ደግሞ በባሕርዩ ሞት፣ ሽረት፤ በመንግሥቱም ኅልፈት፣ ውላጤ የሌለበት ሰማያዊውና ዘላለማዊው ንጉሥ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የነገሠባት የማኅፀነ ድንግል ምሳሌ ነው:: ይኸውም ታላቅና ድንቅ ምሥጢር ሰማያዊው አምላክ ከእመቤታችን መሬታዊ ሰው ሆኖ በኤፍራታ ቤተ ልሔም በከብቶች ግርግም በተገለጠባት የበረከት ዕለት ሰማያውያን ቅዱሳን መላእክት ከምድራውያን ኖሎት (እረኞች) ጋር አንድ ሆነው "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ" (ሉቃ. 2÷14) እያሉ በደስታ ዘምረዋል:: ይህንንም ልዩና ታላቅ የሆነ አዲስ ምስጋና አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ሲናገር "ዮም ሰሐደ መርዔት ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ ንጉሥ በቃለ አሚን"[56] ብሏል:: ይህም ማለት "ዛሬ መላእክትና ሰዎች ንጉሥ ክርስቶስን በታመነ የእውነት ቃል ያመሰግኑት ዘንድ አንድ መንጋ፣ አንድ ማኅበር ሆኑ" ማለት ነው::

ይህ ምሳሌ ከድኅነተ ዓለም ምሥጢር ጋር ያለው ሌላው ጥልቅ ግንኙነት ደግሞ የሰማያውያን ቅዱሳን መላእክት በመሰላሏ አማካይነት ወደ ታች መውረድ አማናዊቷ ሰዋስው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአካላዊ ቃል ርደት (ከሰማየ ሰማያት መውረድና ወደዚህ ዓለም መምጣት) ምክንያት መሆኗን ያመለክታል:: በአንጻሩ ደግሞ የቅዱሳን መላእክት በመሰላሏ አማካይነት ወደ ላይ መውጣትና ማረግ ከክብሩ ተዋርዶና ባሕርይውም ጐስቁሎ የነበረው ሥጋ በርደተ ቃለ እግዚአብሔር መክበሩንና በተዋሕዶተ መለኮት

(56) ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 297:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 48-49፣ *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 337:: Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 38.



የባሕርይ አምላክ መሆኑንም ያስረዳል:: ይህ ታላቅ የሥጋዌ ምሥጢር የተከናወነው በእመቤታችን አማካይነት መሆኑም ወላዲተ አምላክ በነገ ረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻ በግልጥ ያሳያል::[57] ምክንያቱም ከላይ እንደገለጥነው በዕለተ ልደት ሰማያውያን መላእክት ከምድራ ውያን ኖሎት ጋር በአንድነት ሆነው በሕጽነ ድንግል ለተገለጠው አምላክ አምኃ ውዳሴያቸውን ያቀረቡት ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም በተወሰደው ምድራዊ ልደት ወልደ እጓለ እመሕያው በመሆኑ ነው::

ከላይ እንዳየነው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ እመቤታችን በያዕቆብ መሰላል ምሳሌነት መገለጧ ጥልቅ የሆነ የነገረ ድኅነት ትርጓሜ አለው:: ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ይህንን ምሥጢር ሲገልጥ "እንቀጸ ብርሃን መዓርገ ሕይወት"[58] በማለት እመቤታችንን አንቀጸ ብርሃን በተሰኘው ድርሰቱ አመስግኗ ታል:: በዚህም ኃይለ ቃል ወላዲተ አምላክ በኃጢአት ወድቆ የነበረው የሰው ልጅ ክብርን ያገኘባትና ከምድር ወደ ሰማይ፣ ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገረባት አማናዊት የሕይወትና የጽድቅ መሰላል መሆኗን ልብ ይሏል:: ከዚህም ጋር ዕርገተ ሥጋ (የሥጋ ክብር) የተ ፈጸመው በርደተ ቃል (አካላዊ ቃል በማኅፀነ ድንግል ማርያም በማደሩ) ምክንያት ስለሆነ እመቤታችን የሕይወት መሰላል መባሏ ትክክለኛ ነው:: (ዮሐ. 3÷13፤ ማቴ. 21÷9) በዚህ ድንቅ የሥጋዌ ምሥ ጢርም መገለጥ ፍጥረታተ ዓለም በሙሉ መደሰታቸውን በመግለጥ

(57) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 234:: አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *ምልጃ፣ ዕርቅና ሰላም*፣ (አዲስ አበባ፤ አልቦቱ ቤተ ማኅተም፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 52፣ 57:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ 48-49:: *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 96:: Bauer, *The Essential Mary HandBook: A Summary of Beliefs, Devotions and Prayers*, 38. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 35, 43, 57.

(58) ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 402:: ቅዱስ ያሬድ፣ *ዝማሬ መዋሥዕት*፣ (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1994 ዓ.ም.)፣ ገጽ 125:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 381:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን*፣ ገጽ 234-235::

ቅዱስ ያሬድ መሠረተ ሕይወት ወመዝገበ በረከት የሆነችውን እመቤታችንን ሲያመሰግናት «ተፈሥሑ ሰማያት ወተሐሥየት ምድር በልደቱ ለወልድኪ፤[59] ድንግል ሆይ ድንቅ በሚያሰኘው የተዋሕዶ ምሥጢር መድኅን ክርስቶስ ካንቺ በመወለዱ ሰማያት (ቅዱሳን መላእክት) ተደሰቱ፤ ምድርም (ደቂቀ አዳም) ሐሤት አደረጉ» በማለት ዘምሮላታል።

ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም ይህን ታላቅ ምሥጢር በማድነቅ ሲናገር «በእንተ ፍቅረ ሰብእ መጻእከ ውስተ ዓለም፤ ወኵሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ። እስመ አድኃንኮ ለአዳም እምስሕተት ወፈለጥካ ለሔዋን እምዓዘተ እምጻዕረ ሞት»[60] ብሏል። የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም ብርሃነ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅረ ደቂቀ እጓለ እመሕያው አገብሮህ መከራ ልትቀበል በፈቃድህ ልትሞት ወደዚህ ዓለም መጣህ? ሰው ሆነህ በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስነህ ወደዚህ ዓለም በመምጣትህም ፍጥረት ሁሉ ማለትም መላእክትና ደቂቀ አዳም፣ እንስሳትና አራዊት፣ ዕፅዋትና አዝርዕት ሁሉ «ዮም ተወልደ ቤዛ ኵሉ ዓለም፣ ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን፣ ዮም ተወልደ መድኃኔዓለም» እያሉ በአንድነት ፈጽመው ተደስተው አመሰገኑህ ማለት ነው።

ይህንን አስመልክቶ ከሦስቱ የቀጰዶቅያ አባቶች [The Three Cappadocian Fathers] አንዱ የሆነው ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ሲገልጽ **«የክርስቶስ ልደት የመላው ሰው ዘር የልደት ቀን ነው»** ["The Nativity of Christ is the birthday of the whole human race."][61] ሲል መስክሯል።

ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በዘመነ ሥጋዌ ዕርገተ ሥጋ በርደተ ቃል እንደሚፈጸም በመንፈስ ትንቢት


---

(59) ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 403-404። ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 379።

(60) ቅዱስ ኤፍሬም፣ *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 40-42።

(61) Ware, *The Orthodox Way*, 71. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 43.





ሥዕል 2:- ልደተ እግዚእ (የጌታ ልደት)

«ድንግል ሆይ በቤተ ልሔም ካንቺ የተወለደውን መወለድ በጨርቅ የተጠቀለለውንም፤ አድግና (አህያና) ላህም (ላም) በብርድ ወራት እስትንፋስን ያሟሟቁንትም አሳስቢ።»

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 191)

«ላህም ጌታውን እንዲያውቅ የሚያደርገው እርሱ በበረት ተኛ። እንደ ሕፃን አደገ። የሁሉ ጌታ እንደ መሆኑ ሰገዱለት።»

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 200)

አስቀድሞ ሲገልጥ "ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው" (መዝ. 109÷1፤ ማቴ. 22÷43-44) በማለት ተናግሮአል:: ስለሆነም "ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ" የተሰኘው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ረቂቅና ጥልቅ የሆነ የነገረ ድኅነት ምሥጢር የያዘውን ይህንን የቅዱስ ዳዊት ቃለ ትንቢት በተረጐመበት አንቀጽ "መኑ ውእቱ እግዚእከ ኦ ነቢይ ወንጉሥ ዘእንበለ ወልደ እግዚአብሔር ዘተወልደ እምወለትከ:: መኑ ውእቱ ዘይቤሎ ንበር በየማንየ ዘእንበለ አሁቡ ሰማያዊ ዘወለደ እምቅድመ አዳም:: ወዘይቤሎሰ ንበር በየማንየ አኮ በእንተ መለኮተ ወልዱ ምስሌሁ አላ በእንተ ትሰብእተ ወልዱ እንተ ይእቲ ሥጋ ዚአከ:: ዘኢነበረ ከመ ያንብር ይቤ ዘንተ:: እስመ ለዘይነብርሰ ኢይደልዎ ብሂለ ንበር እስመ ኀቡር ውእቱ ለዝሉፉ:: በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም::" ብሏል::

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ "በዛቲ ዕለት ይደልወከ ኦ ነቢይ ከመ ትትፌሣሕ ፈድፋደ እምኵሎሙ ቅዱሳን እስመ ነበረ ወልደ ወለትከ በየማነ አቡሁ ሰማያዊ በሥጋ ዘነሥአ እምኔሃ:: ወተለዓለ መንግሥትከ እምሀገረ ኢየሩሳሌም ውስተ ጽርሐ አርያም ወተመይጠ ጽዋዔ ስሙ እምብሂለ ንጉሠ እስራኤል ኀበ ብሂለ አምላከ እስራኤል:: ወአንተሰ ሰብሖ ለወልድከ በሥጋሁ ወአምላክከ በህላዌሁ እንዘ ትብል ዐረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ ወወሀብከ ጸጋከ ለእጓለ እመሕያው::"[62] በማለት ነቢየ እስራኤል ቅዱስ ዳዊትን በመጽሔተ ምሥጢር እያየ፣ በቃለ አንክሮ እያነጋገረ ከሰው ልጆች ኅሊናና ከመላእክት አእምሮ በላይ የሆነውን ረቂቅና ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር ያደንቃል::

ከላይ የጠቀስነው የሊቁ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢሩም ነቢየ አምላክ፣ ንጉሠ እስራኤል የሆንክ ቅዱስ ዳዊት ሆይ ጌታዬ ብለህ በመንፈስ ትንቢት የተናገርህለት ከአንተ ባሕርየ ዘርዕ ከተገኘችው

(62) አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ ["Abba Giyorgis Di Sagla"]፣ "መጽሐፈ ምሥጢር" ["Il Libro Del Mistero"] *CSCO*, 238-239. አባ ጊዮርጊስ፣ "መልክዐ ሥዕል"፣ *መጽሐፈ ሰዓታት ወመዝገበ ጸሎት* (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 255:: Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 36. *መዝሙረ ድንግል*፣ ገጽ 90:: ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መሪጌታ)፣ "እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ"፣ ገጽ 11፣ 13::



ከቅድስት ድንግል እመቤታችን ከተወለደው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ በቀር ሌላ ማነው? ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስንስ ከአዳም በፊት ቅድመ ዓለም ከባሕርይው ያለ እናት ከወለደው ከባሕርይ አባቱ ከአብ በስተቀር ማን በቀኜ ተቀመጥ ይለዋል? ዳግመኛም እግዚአብሔር አብ ልጁን ወልድን በቀኜ ተቀመጥ ያለው ባሕርየ መለኮቱን ሲያይ አይደለም:: ይልቁንም ወልደ እግዚአብሔር ከዳዊት ወገን ከሆነችው ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ የነሣውን ባሕርየ ትስብእቱን ሲያይ ነው እንጂ:: በየማነ አብ በቅድምና ያልነበረ ሥጋን በአብ ዕሪና (ክብር) ያኖረው ዘንድ ይህን አለ:: በቅድምና በየማነ አብ ይኖር የነበረው ወልድን ግን ድኅረ ዓለም በአብ ዕሪና (ክብር) ተቀመጥ ይሉት ዘንድ አይገባም:: ምክንያቱም እርሱ ዘወትር በየማነ አብ ይኖራልና:: ቅድመ ዓለም በየማነ አብ እንደነበረ ሁሉ ማዕከለ ዓለምም ሆነ ድኅረ ዓለም ለዘላለም በአብ ዕሪና (ክብር) ይኖራል::

ዳግመኛም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ሆይ በዚህች ቀን ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ፈጽመህና አብዝተህ ልትደሰት ይገባሃል:: ከአንተ ዘር ከምትሆን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ የተወለደው ከእርሷ በነሣው ሥጋ በሰማያዊው አባቱ ቀኝ በክብር መቀመጥን ገንዘብ አድርጓልና:: በዚህም ምክንያት ግዛትህ ከምድራዊቷ ኢየሩሳሌም ወደ ጽርሐ አርያም ከፍ ከፍ ብሏልና፤ ዳግመኛም የስሙ መጠሪያ የእስራኤል ንጉሥ ከመባል ይልቅ የእስራኤል አምላክ ወደ መባል ተመልሷል:: ስለዚህም አንተ በሰውነቱ ልጅህ፣ በመለኮቱ ደግሞ አምላክህ የሚሆን እርሱን ነፍሳትን ማርከህ ወደ ሰማይ በክብር ዐረግህ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስንም ለሰው ልጆች ሰጠህ እያልክ አመስግነው ማለት ነው::

ከላይ እንደገለጥነው የነቢየ እግዚአብሔር የቅዱስ ዳዊት ቃለ ትንቢት በኃጢአት ወድቆ፣ ከክብሩ ተዋርዶ የነበረው የሰው ልጅ ወደ

ቀደመ ክብሩ መመለሱንና የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ኃይለ ቃል ነው። (2ኛ ጴጥ. 1÷4) በዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዳዊት ዘር ከሆነችው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ የነሣው ሥጋ በክብር ወደ ሰማይ ማረጉንና በየማነ አብ (በአብ ዕሪና በምልዓት፣ በጌትነት፣ በክብር) መቀመጡን ልብ ይሏል። በዚህም ረቂቅ የሥጋዌ ምሥጢር ሥጋ በዘባነ ኪሩብ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚመለክና በአንድ ምስጋናም የሚመሰገን ሆኗል። ምክንያቱም የዳዊት መንግሥት ከምድራዊቷ ኢየሩሳሌም ወደ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ከፍ ከፍ ብሏልና። በዚህም ልዩ ምሥጢር ንጉሠ እስራኤል የሚለው ስያሜ አምላከ እስራኤል በሚለው አዲስ ስያሜ ተተክቷል። ሕያወ ባሕርይ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደኃራዊ በሚሆን ምድራዊ ልደቱ ወልደ ዳዊት፣ ቀዳማዊ በሚሆን ሰማያዊ ልደቱ ደግሞ አምላከ ዳዊት ይባላል።[63]

ዳግመኛም ይህንን ታላቅ ምሥጢር አስመልክቶ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ሲናገር «ወእመሂ ነበረ በየማነ አቡሁ በክልኤ ገጽ እምኮነ ትርብዕተ ወአኮ ትሥልስተ። በከመ ኢያስተርእዮ በምድር በምንታዌ፤ ከማሁ ኢነበረ በየማነ አቡሁ በክልኤ ግጻዌ። በከመ ኢኀቀፈት እሙ በእብራኢሃ በክልኤ አርአያ፤ ከማሁ ኢያንበሮ አቡሁ ዲበ ሰረገላሁ በክልኤ ፍኖ»[64] ብሏል። ይህም ማለት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን የማዳን ሥራውን ፈጽሞ በመላእክት ምስጋና፣ በሰማይ ደመና በክብር ባረገ ጊዜ አስቀድሞ በተዋሕዶ አንድ እንደነበረ እንጂ ሁለት አልሆነም። ይህማ ቢሆን ኖሮ በሦስትነት ላይ ርባዔን (አራትነትን)፣ በአንድነት ላይ ምንታዌን (ሁለትነትን) ባመጣ ነበር። ስለሆነም ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት በዚህ ዓለም ሥጋን ተዋሕዶ ተገልጦ ሲመላለስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደ ነበር እንጂ

[63] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፣ ["Il Libro Del Mistero"], ገጽ 238-239*። ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 387*። McNamara, *Mother of the Redeemer: Aspects of Doctrine and Devotion*, 71-76። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ አርጋኖን፣ ገጽ 157*።

[64] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፣ ["Il Libro Del Mistero"], ገጽ 233*።



ሁለት አካል፣ ሁለት ባሕርይ፣ ሁለት ፈቃድ፣ ሁለት ግብር እንዳልነበረው፤ እንዲሁም ሁሉ በአባቱ ቀኝ በአንድነት እንጂ በሁለትነት አልተቀመጠም። ዳግመኛም እናቱ ቅድስት ድንግል እመቤታችን በአንድነቱ እንጂ በሁለትነት በክንዶቿ እንዳልታቀፈችው ሁሉ፤ እንዲሁም ቅድመ ዓለም ያለ እናት የወለደው የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ በሁለት መንበር አላስቀመጠውም ማለት ነው።

በመቀጠልም ይኸው ሊቅ ሲያስረዳ «ኢነበረ ትስብእቱ ዕሩቀ መለኮቱ፤ በከመ ይነብር ወልድ በየማነ አቡሁ እሳ ነበረ በ፩ አካል እንበለ ቱሳሔ ወበ፩ ራእይ ዘእንበለ ውዓጤ። ወበእንተዝ ሰብሕዎ መላእክት ለእንግዳ ዘመጽአ ኀቤሆሙ ወዝውእቱ ትስብእተ መለኮቱ ለዋሕድ። አወፈይዎ ስብሐተ ዘዕሟድ ዘዘዕሬ ያቄርቦ ለመለኮቱ። ወኢያወፈይዎ ካዕበ ስብሐተ ከመ ኢይኩን ተውሳከ እምዕሶ እምስብሐተ መለኮት ዘዕሟድ ከመ ኢይትነከር ተሰብኦ እምዝምሬተ ኃይል ዘኢያስተርኢ። ወበእንተዝ ንሕነኒ ናምዕኮ በ፩ አካል እንበለ ሴዕዮ ወበ፩ ዝምሬት ዘእንበለ ፍዕጠት»[65] በማለት ተናግሮአል።

የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢርም «ሥጋ ከመለኮት ተለይቶ ብቻውን አልነበረም። ይልቁንም ያለ መጨመርና ያለመለወጥ በአንድነቱ በየማነ አብ ተቀመጠ እንጂ። ስለሆነም በተዋሕዶተ ቃለ እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ የሆነ ሥጋን ቅዱሳን መላእክት አመሰገኑት። በዚህም ዘወትር ለአምላክነቱ፣ ለጌትነቱ የሚያቀርቡትን የተለመደውን ምስጋና አቀረቡለት እንጂ ከዚህ የተለየ ሌላ አምልኮና ምስጋና ያቀረቡለት አይደለም። ስለዚህ እኛም ያለመለየት በአንድነቱ እናመልከዋለን» ማለት ነው። በአጠቃላይ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ምሥጢረ ሥጋዌ የምሥጢራት ሁሉ ርእስ በመሆኑ የዚህ ታላቅና ድንቅ ምሥጢር ፍጻሜ መሠረት ወላዲተ አምላክ መሆኗን ይገነዘቧል። ይኸውም ሊቁ «ዝውእቱ ሰዋስወ ሃይማኖትነ ዘያበጽሐነ እምድር ውስተ አርያም»[66] ብሎ እንደተናገረው ይህ

[65] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ["Abba Giyorgis Di Sagla"]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፤ ["Il Libro Del Mistero"]፣ ገጽ 233-234*።

[66] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ["Abba Giyorgis Di Sagla"]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፤ ["Il*

ፈንታ የተሠዋው በግ የአማናዊው በግዐ መሥዋዕት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፣ የመሥዋዕቱ በግ ቀንዶች የተያዘበት ዕፀ ሳቤቅ የአማናዊቷ እሙ በግዐ ነባቢ (የሚናገር በግ) የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው::(68) ዕፀ ሳቤቅ ማለት ሐረግ የበዛበት ጉንድ (ዕፅ) ማለት ነው:: አማናዊቷ ዕፀ ሳቤቅ ወላዲተ አምላክም የንጽሕናዋና የቅድስናዋ፣ የምስጋናዋና የክብሯ ሐረግ የበዛ አማናዊት እሙ በግዐ ነባቢ ናትና:: ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይህንን የድኅነተ ዓለም ምሥጢር በተረጐመበት አንቀጽ «ወትቤሎ ማርያም ለአፈ ጋይ እርእያስ ተገብረ ወፍፌሁስ ኢኮነ ዘእንበለ ይእዜ:: ... ወኑ ፈሰፃ ለዕፀ ሳቤቅ ከመ ትስድ በግዐ ዘእንበለ ፈካቤ:: እብልስ በግዐ ዘቤዘዎ ለይስሐቅ እርእያ ወአምሳሊ:: ወበግዐ ዘሀሎ ውስተ ከርሥየ በግዐ ዘበአማን ዘበእንቲአሁ ይቤ ኢሳይያስ ወዩእ ይጠባሕ ከመ በግዕ፤ ወከመ በግዐ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርፆ»(69) ሲል ተናግሯል:: በዚህም በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳል የተገለጸው የድኅነተ ዓለም ምሥጢር በድንግል ማርያም እንደተፈጸመ ልብ ይሏል::

ከላይ የጠቀስነው የሊቁ ኃይለ ቃል ምሥጢራዊ ትርጓሜ እመቤታችን ድንግል ማርያም አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና የመጽነሷን ነገር በጠየቃት ጊዜ ከላይ የተመለከትነውን አማናዊ ምሳሌ ጠቅሳ የተናገረችው ቃለ ሃይማኖት ነው:: ዕ ትርጓሜውም ምሳሌ ተገለጠ ፍጻሜው ግን ከአሁን በቀር አልሆነም:: ዕፀ ሳቤቅን ያለ ሩካቤ በግን ትወልድ (ታስገኝ) ዘንድ ማን አደረጋት? ያደረጋት ማን ነው? ይስሐቅን ከመታረድ ያዳነውና ከሞት የታደገው በግ ምሳሌና መርገፍ ነበር:: በማኅፀኔ ያለው አማናዊው የመሥዋዕት በግ ግን እርሱ ቤዛ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ስለ እርሱም ልዑል ቃል

(68) Daniel, *Blessed Virgin Mariam*, 27. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 596-598::

(69) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ["Abba Giyorgis Di Sagla"]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፤ ["Il Libro Del Mistero"]*፣ ገጽ 8:: Brock, *Bride of Light*, 42, 47. ቅዱስ ያሬድ፣ *ዝማሬ መዋሥዕት*፣ ገጽ 55-56:: አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ ["Abba Giyorgis Di Sagla"], *ዕንዚራ ስብሐት ["The Lyre of Glory"]*, 66.



ኢሳይያስ "ለመታረድ እንደሚነዳ በግ በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል ጠቦት አፉን አልከፈተም» (ኢሳ. 53÷7፤ የሐዋ. ሥራ 8÷33-37) ብሎ የተናገረለትና የመሰከረለት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም አስቀድሞም ሆነ ወደፊትም በሥነ-ፍጥረት ታሪክ ውስጥ በግ ያስገኘች ዕፅ እንዳልነበረች ሁሉ፤ ከእርሷ በፊትም ሆነ ከእርሷ በኋላ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ የፀነሰችና የወለደች ከድንግል እመቤታችን በቀር ማንም ሴት የለችም፣ ወደፊትም አትኖርም:: በዚህም ምክንያት ዕፀ ሳቤቅ ለአማናዊቷ እሙ በግዐ ለወላዲተ አምላክ ምሳሌ መሆኗን ይገነዘቧል::

ከዚህም ጋር ከዕፀ ሳቤቅ የተገኘው ፀዓዳ በግ በሞሪያ ተራራ በተዘጋጀው የእንጨት መሠዊያ ላይ በይስሐቅ ፈንታ መታረዱ፤ ከአማናዊቷ ዕፀ ሳቤቅ ከድንግል ማርያም የተወለደው አማናዊው በግዐ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስም በቀራንዮ ተራራ ዕፀ ሕይወት በሆነው በመልዕልተ መስቀል ለመሠዋቱ አማናዊ ምሳሌ ነው:: በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚጸለየው የቅዱስ ባስልዮስ የሊጦን ምስጋናም "ወካዕበ ናአተበቍዓ ለአምላከ ምሕረት ዘረዳኦ ለአብርሃም አመ ይቀትሎሙ ለነገሥት፤ ዘአድኃኖ ለይስሐቅ እምነ መጥባሕት ... ፤ ዳግመኛም አብርሃም ለአምስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ ነገሥተ ኮሎዶጎሞርን ድል ባደረገ ጊዜ የረዳኸው፤ ይስሐቅንም ቤዛ መድኃኒት የሚሆነው በጉን ከላይ ከሰማይ አዘጋጅተህ አውርደህ ከመታረድ (ከመሞት) ያዳንከውንና የታደግኸውን የምሕረት አምላክ አንተን ዳግመኛ እንማልዳለን»(70) ይላል:: *በዚህም ከኅቱም ጉንድ የተገኘው ይህ በግ ይስሐቅን ከመታረድ (ከሞት) እንዳዳነው ሁሉ፤ ከኅቱም ማኅፀነ ድንግል የተገኘው በግዐ ሕይወት ወቍርባነ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስም አዳምን ከነልጆቹ በወርቀ ደሙ ዋጅቶ ሕይወትን በሚሰጠው ሞቱ ከሞት ማዳኑን አስረግጦ ይመሰክራል::

ከላይ እንደተመለከትነው መፍቀሬ እግዚአብሔር የሆነው አብርሃም በግዐ መሥዋዕቱን በዱር ውስጥ አይቷል:: ይህንን አስመልክቶም ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ፤ ወረከብናሁ ውስተ

(70) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 60:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ["Abba Giyorgis Di Sagla"]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፤ ["Il Libro Del Mistero"]*፣ ገጽ 91::

ፃዐ ገዳም፤ እነሆም በኤፍራታ ሰማነው፣ በዱር ውስጥም አገኘነው" (መዝ. 131÷6) በማለት ለአዲስ ኪዳን የሥጋዌ ምሥጢር ሰጥቶ ዘምሮአል:: የዚህም ቃለ ትንቢት ፍጻሜ ምሥጢራዊ ትርጓሜው እነሆ መሲሕ ክርስቶስን በኤፍራታ ቤተልሔም ተወልዶ፣ በጨርቅ ተጠቅልሎ፣ በበረት ተጥሎ በግዕዘ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው::: በከብቶች ማደሪያ በግርግም ተኝቶ አገኘነው ማለት ነው:: ሌላው ምሥጢር ደግሞ ቤዛ ይስሐቅ የሆነው በግ በሞሪያ ተራራ መሠዋቱ፤ ቤዛ አዳም፣ ቤዛ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ተራራ ለመሠዋቱ ምሳሌ ነው:: ልበ አምላክ የተባለው ቅዱስ ዳዊት "እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር፣ ዘመን ሳይቆጠር በፊትም ንጉሥ ዘኢይደሰ ይምዋ (የማይሾሙትና የማይሽልሙት፣ የማያነግሡት) የባሕርይ ንጉሥ ነው:: የሰው ልጆችን ድኅነትም ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከባሕርዩ የወለደውን አንድያ ልጁን ሂድ፣ ውረድ፣ ተወለድ፣ ተሰቀል፣ ሙት በማለቱ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ተራራ አደረገ" ሲል እንደመሰከረ:: (መዝ. 73÷12)

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ከኅቱም ማኅፀን የተገኘውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት ሥራ በተረጐሙበት አንቀጽ አማኑኤል አምላካችን ከባዱን መስቀል ተሸክሞ ከልጠስጥራ ወደ ቀራንዮ ተራራ መጓዙ፣ ይስሐቅ ከኅቱም ጉንድ የተገኘው በግ የተሠዋበትን ዕፅ ተሸክሞ ወደ ሞሪያ ተራራ የመውጣቱ ምሳሌ አማናዊ ፍጻሜ ነው ብለዋል:: በመሆኑም በዘመነ አበው የተገለጠው ይህ ኅብረ አምሳል በኋለኛው ዘመን መሲሕ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በቀራንዮ መስቀል ተሰቅሎና ሙቶ የድኅነተ ዓለም ሥራን እንደሚፈጽም የሚያሳይ ምሥጢራዊ መጽሔት ነው:: በዚህም መድኅነ ዓለም ቤዛ አዳም የሆነው መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በክቡር ደሙ ፈሳሽነት በዔዋዌ (በምርኮ) የነበሩትን ነፍሳት ከኃጢአት ባርነት፣ ከዲያብሎስ ቁራኝነትና ከሞት ተገዥነት



እንዳዳናቸውና ነጻ እንዳወጣቸው በግልጽ እንረዳለን፣ እንገነዘባለን::(71)

ከዐበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ልዑለ ቃል ኢሳይያስ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ሲገልጥ "እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ፤ የድኅነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን" (ኢሳ. 53÷5) በማለት ተናግሮአል:: ከላይ በገለጥነው ምሳሌ መሠረት በይስሐቅ ፈንታ የተሠዋው በግ ፀዓዳ መሆኑ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ንጹሐ ባሕርይ የሆነ አምላክ መሆኑን ያመለክታል:: ምክንያቱም ጌታችን ፀዓዳ በመለኮቱ ነውና:: ስለሆነም ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ፣ በደል (ወንጀል) የሌለበት ቅዱስ አምላክ ስለ እኛ መርገም ተላልፎ የተሰጠልን ማኅየዊ በሆነው ሞቱ የእኛን ኃጢአትና መርገም ወስዶ የእርሱን ሕይወትና በረከት ለእኛ ለመስጠት ነው:: ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "መፍቀሬ ሰብእ አቀ ረበነ ኅቤሁ:: ዘዚአነ ሞተ ነሥአ፤ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ፤ ሰውን እስከ መስቀል ሞት የወደደ እርሱ የእኛን ሞት ለራሱ ሞቶ፣ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን÷ በዚህም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታረቀን"(72) እንዳለ::

ከዚህም ጋር መጽሐፍ "ወቦአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ኵሉ ጸዋትወ መከራ እንተ ባቲ አመከረነ ጸላዒ፤ ጥንተ ጠላታችን የሆነው ዲያብሎስ አካለ ከይሲን መሰወሪያ፣ ልሳነ ከይሲን መናገሪያ አድርጎ እንዳሳተን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ በሥጋ ብእሲ ተሰውሮ አዳነን" በማለት ያስገነዝባል:: ዳግመኛም ቅዱስ ዮሐንስ ሐዋርያ "ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኵሉ ኃጣውኢነ፤ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ መስቀል የፈሰሰው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደሙ ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል፣ ከርኩሰታችንም ሁሉ ይቀድሰናል" (1ኛ ዮሐ. 1÷7) ሲል መስክሮአል::

---

(71) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰርጋዌ*፣ ገጽ 158:: አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 596:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር*፣ *["Il Libro Del Mistero"]*፣ ገጽ 233::

(72) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 151-152::

በዘመነ ሐዲስ በተገለጠው አማናዊው መሥዋዕት ዓለም ሁሉ ከፍዳና ከመርገም መዳኑ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ሚና በሚገባ ያስረዳል:: ይህንን አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ሲናገር «ኦ ድንግል ዘፈረዩት ለክነተ ይትበላዕ ወዘመንቀዕተ ለክነተ ይሰተይ፤ ድንግል ሆይ መብልዐ ጽድቅ የሆነውን ኅብስተ ሕይወት ቅዱስ ሥጋውን፣ ስቴ መድኃኒት የሆነውን ማየ ሕይወት ክቡር ደሙን ያስገኘሽልን አንቺ ነሽ» ብሏል::

ከዚህም ጋር «ኦ ኅብስት እንተ እምኔኪ ለለ ይበልዑ እምኔሁ በአሚን ዘይሁብ ሕይወተ ወመድኃኒተ፤ የሥጋዌውን ምሥጢር አውቀውና ተረድተው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን አምነው ለሚቀበሉ ሁሉ ከአንቺ የተገኘው ኅብስት ሕይወተ ነፍስን፣ ድኅነተ ነፍስን የሚያድል ነው::» ዳግመኛም «ኦ ጽዋዕ እንተ እምኔኪ ለለ ይሰትዩ እምኔሁ በአሚን ዘያጕሥዕ ጥበበ:: ወይሁብ ሕይወተ፤ ድንግል ሆይ ካንቺ የተገኘው ጽዋ ሥጋዌውን በሚገባ ጠንቅቀው ተረድተው፣ ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ደመ መለኮት እንደሚሆን ፈጽመው አምነው ለሚጠጡት ሁሉ በልሳነ ሥጋ ቋንቋ የሚያናግር፣ በልሳነ ነፍስ ደግሞ ምሥጢር የሚያስተረጉም፤ አንድም ሕይወተ ሥጋን ሕይወተ ነፍስን የሚያድል ነው» በማለት የምሥጢሩን ምልዓትና ስፋት፣ ርቀትና ምጥቀት ያደንቃል::[73]

## 2.2 የመጻሕፍተ ቅዳሴያት አስተምህሮ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከአምስቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ ነች:: በጉባኤ ኬልቄዶን የተወሰነውን የሁለት ባሕርይ ትምህርት ሳይቀበሉ ወልድ ዋሕድ በሚለው ሐዋርያዊ ትምህርት ጸንተው የሚኖሩት እነዚህ አምስት አብያተ ክርስቲያናት ኢትዮጵያ፣ ግብፅ፣ አርመን፣ ሶርያና ሕንድ ናቸው:: ስለሆነም ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንታውያን

(73) *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 162-164::



አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ በመሆኗ የታሪክ ምሁራን «ኢ-ኬልቄዶናውያን ከሆኑት ከአምስቱ የምሥራቅ ኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ብዙ ተከታዮች ያሏት ታላቋ ቤተ ክርስቲያን» ["The largest of the five non-Chalcedonian Eastern Churches"][74] በማለት ይመሰክሩላታል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ በተላለፈላት ሐዋርያዊ ውርስ መሠረት ጥንታዊውን ሥርዓተ አምልኮ ለረጅም ምእተ ዓመታት ይዛና ጠብቃ የኖረች ቤተ ክርስቲያን ናት:: በመሆኑም ሥርዓተ ቅዳሴ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥጋ ወደሙን ምሥጢር ዘወትር የምታከብርበት ታላቅና ሰማያዊ ሥርዓት ነው:: ስለሆነም ሥርዓተ ቅዳሴ የክርስትና እምነት ሥርዓተ አምልኮ ዋነኛው ማዕከል በመሆኑ ምሥጢረ ቅዱስ ቁርባን ለቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓተ አምልኮዋ ሁሉ አክሊል ወይም ጉልላት ነው::[75]

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያላት በመሆኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዘወትር ሥርዓተ ቅዳሴዋ ከምታስባቸውና ከምታከብራቸው ቅዱሳን ሁሉ የበለጠ ልዩ ሥፍራ አላት:: ከላይ ቀደም ብለን በመቅድማችን ላይ እንዳወሳነው በዜና አበው የትምህርት መስክ የተነሡ አያሌ ቅዱሳን አበው ስለ ነገረ ማርያም አምልተውና አስፍተው ያስተማሩት ትምህርት፤ እንዲሁም

(74) The Interim Secretariat Oriental Orthodox Conference, ed., *The Oriental Orthodox Churches Addis Ababa Conference* (Addis Ababa: Artistic Printers, 1965), 3. Aymro Wondemagegnehu and Joachim Motovu, *The Ethiopian Orthodox Church,* xiii.

(75) Mercer, *The Ethiopic Liturgy: Its Sources, Development and Present Form,* 46, 71, 79-85. D. O. Haulon, *Features of the Abyssinian Church* (London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1946), 36, 39. F. L. Cross, ed. *The Oxford Dictionary of the Christian Church,* 2nd ed. (London: Oxford University Press, 1974), 830. Sergew Hable-Selassie, "The Establishment of the Ethiopian Church," *The Church Of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life,* 1-6. አያሌው ታምሩ (ሊቀ ጠበብት)፣ *የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፣* (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1952 ዓ.ም.)፣ ገጽ 205::

በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉት ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ላይ የተረቀቀው የሃይማኖት ውሳኔ የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ቅዳሴ ንባብና ምሥጢር እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::(76)

አብዛኞቹ የሥርዓተ ቅዳሴ ሊቃውንት እንደሚመሰክሩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ጥንታዊነቱ ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የታወቀና የተረዳ እውነታ መሆኑን ይገልጻሉ:: በታሪክ እንደምናነበው አያሌ የሥርዓትና የአምልኮ መጻሕፍት ወደ ግዕዝ ቋንቋ እንደተመለሱ (እንደተተረጐሙ) ይታወሳል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ሰማያዊ ጸጋ አክብራና ጠብቃ እስከ ዛሬ ድረስ ስትጠቀምበት ኖራለች፣ ወደ ፊትም ስትጠቀምበት ትኖራለች:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሁን ባላት የመንፈሳዊ አገልግሎት ደረጃ የምትገለገልባቸው አሥራ አራት ቅዳሴያት አሏት:: አብዛኞቹ የሥርዓተ ቅዳሴ ሊቃውንት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ቅዳሴ [Pre-Anaphora] እና የፍሬ ቅዳሴ [Anaphora] አገልግሎት የሚታወቀው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበረው ከቅዱስ ፍሬምናጦስ ወይም አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ይገልጻሉ::(77)

(76) Archbishop Yeshaq, *The Structure and Practice of the Ethiopian Church Liturgy,* i, 12. O' Carroll, *Theotokos: A Theological Encyclopedia of the Blessed Virgin Mary,* 121, 165, 186f. Tambasco, *What are they Saying about Mary?*, 66.

(77) ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዘወትር ሥርዓተ አምልኮዋ የምትገለገልባቸው አሥራ አራቱ ቅዳሴያት:- ቅዳሴ ሐዋርያት፣ ቅዳሴ እግዚእ፣ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ (ፍቁረ እግዚእ/ ወንጌላዊው)፣ ቅዳሴ ማርያም፣ ቅዳሴ ሠለስቱ ምዕት (318ቱ የጉባኤ ኒቅያ አበው ሊቃውንት)፣ ቅዳሴ አትናቴዎስ፣ ቅዳሴ ባስልዮስ፣ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፣ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዳሴ ቄርሎስ፣ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ቅዳሴ ዲዮስቆሮስና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ (ዘአርማንያ) ናቸው:: H. M. Hayatt, *The Church of Abyssinia* (London: Luzac and Co., 1928), 95. Marcos Dauod, trans., *The Liturgy of the Ethiopian Church,* Revised by M. Hazen (Cairo: Egyptian Books Press, 1959), 69, 98, 110, 103, 153-154, 174, 197, 218, 233, 249, 263, 279, 294, 304. E. Hammerschimidt, *Studies in the Ethiopian Anaphoras* (Berlin: Akademic - Verlag, 1961), 41-43. Mercer, *The Ethiopic Liturgy: Its Sources, Development, and Present Form,* 5-6, 95. *መጽሐፈ ቅዳሴ*፣ ገጽ 5::



የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ ይዘት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን እነዚህም:- 1ኛ. የዝግጅት ክፍል (ግብዓተ መንጦላዕት)፣ [Preparatory Service] 2ኛ. ሥርዓተ ቅዳሴ [Pre-Anaphora] እና 3ኛ. ፍሬ ቅዳሴ [Anaphora] በመባል ይታወቃሉ:: የመጀመሪያው ክፍል የሥርዓተ ቅዳሴው የመግቢያ ዝግጅት ክፍል ነው:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በውስጡ የተለያዩ ጸሎታትንና ቡራኬያትን፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባባትንና ጸሎተ ሃይማኖትን (የሃይማኖት ምስክርነት) የያዘ ነው:: ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ፍሬ ቅዳሴ ሲሆን ይህም የሥርዓተ ቅዳሴው ዋነኛው ክፍል ነው:: ይኸውም በውስጡ ሥርዓተ ጸሎት ዘምሥጢረ ቁርባንና ጸሎተ ፈትቶ፣ እማሬያትንና ቡራኬያትን ይይዛል::(78)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ "ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" (ሉቃ. 22÷19)፣ 1ኛ ቆሮ. 11÷24) ብሎ በሰጠው አምላካዊ መመሪያ መሠረት፤ እንዲሁም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ" (1ኛ ቆሮ. 11÷26) ሲል እንዳስገነዘበው በዘወትር የሥርዓተ ቅዳሴ አምልኮዋ ጊዜ "ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ፣ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ፤ አቤቱ ማኅየዊት የምትሆን ሞትህንና ክብርት የምትሆን ትንሣኤህን እንናገራለን፤ እንዲሁም ዕርገትህንና ዳግመኛ በግርማ መለኮት መምጣትህንም እናምናለን"(79) እያለች የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማማተ መስቀል፣ ሞቱንና ትንሣኤውን ታስባለች፣ ትመሰክራለችም::

(78) ያሬድ ካሣ (መጋቤ ብሉይ)፣ *የቅዳሴ ሥርዓት*፣ ክፍል ፩፣ (አዲስ አበባ፤ አሰግ-ሉሲ ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም.)፣ ገጽ 3-4:: Nikolaus Liesel, *The Eucharistic Liturgies of the Eastern Churches,* trans. David Heimann (Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1963), 38, 40-50. Hammerschimidt, *Studies in the Ethiopian Anaphoras,* 50-60. Mercer, *The Ethiopic Liturgy; Its Sources, Development and Present From:* 295-373. For further details on each texts, See Daoud, trans., *The Liturgy of the Ethiopian Church,* 5-59. Mercer, *The Ethiopic Liturgy: Its Sources, Development and Present Form,* 295-273, 141-220.

(79) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 125::

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዘወትር ሥርዓተ ቅዳሴዋ ኅብስቱና ጽዋው በካህናት ጸሎትና ቡራኬ አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተለውጦ ከቅድስት ድንግል ማርያም በኤፍራታ ቤተ ልሔም የተወለደው፣ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ የተጠመቀው፣ መከራ መስቀልን ታግሦ ስለእኛ የታመመው፣ የሞተውና የተነሣው፣ በክብር ወደ ሰማይ ያረገው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ እንደሚሆን ታምናለች፤ ታስተ ምራለችም:: (ማቴ. 26÷26-28፤ ሉቃ. 22÷19-20)

ይህንን አማናዊ ምሥጢር በመግለጥ የቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎት "ይህ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሁላችን እመቤት ከሆነችውና በድንጋሌ ሥጋ፣ በድንጋሌ ነፍስ ከጸናችው ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውና ከባሕርየ መለኮቱ ጋር በተዋሕዶ አንድ ያደረገው፤ ስለ እኛ ድኅነት ለመከራ፣ ለሕማምና ለሞት አሳልፎ የሰጠው ኅብስተ ሕይወት፣ ጽዋዐ መድኃኒት መሆኑን እስከ መጨረሻይቱ ሕቅታ ድረስ እናምናለን፣ እናሳምናለን::[80] በማለት በአጽንኦት ይመሰክራል::

የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ ዋና ዓላማ የድኅነተ ዓለም ሥራ የተፈጸመበትን የሥጋዌ ምሥጢር ማዘከርና ምእመናንን የዚህ ታላቅና ሰማያዊ ማዕድ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ መጋበዝ በመሆኑ መሠ ረተ ሕይወት የሆነችው ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻ በግልጥ ያሳያል:: ስለሆነም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር የድኅነት መሣሪያው አድርጎ ስለመረጣትና ስላከበራት በኦርቶዶክሳውያን ሥርዓተ ቅዳሴ ውስጥ ልዩ የሆነ ሥፍራ አላት::

ከቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ የመግቢያ ጸሎት ክፍል አንዱ እመቤታችንን ኅብስተ ሕይወት ዘሰዓስም የተባለ ጌታ የተገኘባት

[80] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 120::



አማናዊት የወርቅ መሶብ መሆኗን ያወሳል፣ ይመሰክራል::[81] ይኸውም በመብል ምክንያት የወደቀውና የሞተው የሰው ልጅ ትንሣኤ ልቡናን አግኝቶ ሕያው እንዲሆን መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል መብልዐ ጽድቅ የሆነውን ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶአል፣ ስቴ መድኃኒት የሆነውን ማየ ሕይወት ደሙንም አፍስሶአል:: በመሆኑም ይህ አማናዊ የሕይወት ማዕድ የተገኘው ከድንግል ማርያም በመሆኑ እመቤታችን ምክንያተ ድኅነት ናት:: ረኃበ ነፍስ ያለባቸውን ሁሉ የሚያጠግበውን፣ ጽምዐ ነፍስ የያዛቸውን ሁሉ የሚያረካውንና የማይለ ወጠውን ይህን የሕይወት ማዕድ ያፈራችው እሙ ሕይወት ድንግል ማርያም መሶበ ወርቅ ዘመና መባሏም ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን ለመግለጥ ነው::

ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም የድኅነተ ዓለም ጉዞ ለተ ከናወነበት ለሥጋዌ ምሥጢር መሠረት መሆኗ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ የሚያስረዳና የሚያረጋግጥ ሌላው ምስክር ነው:: ይህንን ምሥጢር አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን የቅዳሴ መጽሐፍ ሲገልጽ እመቤታችንን ፍሕመ እሳትና መዓዛ ዕጣን በሚዋሐዱበት በማዕጠንተ ወርቅ ይመስላታል:: የዚህ ምሳሌ ትርጓሜ ምሥጢርም ,ማዕ ጠንት የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ፤ ወርቁ የንጽሕናዋ፣ የቅድስናዋ ምሳሌ፤ ዕጣኑ የትስብእት ምሳሌ፤ ፍሕመ እሳት ደግሞ የእሳተ መለኮት ምሳሌ ነው:: በዚህም መፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር ማኅደረ እግዚአብሔር ከሆነው ከአብርሃም ባሕርይ ለተዋሕዶ የመ ረጣትና ያዘጋጃት ልዩ የድኅነት መሣሪያው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መሆኗን ልብ ይሏል::[82]

ይኸውም ከእርሷ ባሕርይ የተገኘው መድኅን ክርስቶስ መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ፤ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን

[81] መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 39:: ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 388:: ቅዱስ ያሬድ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 408:: ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 174:: Mercer, *The Ethiopic Liturgy: Its Sources, Development and Present Form*, 304.

[82] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 199-201:: መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 63:: ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 326-332:: መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 70-71::

የሚያድል፤ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ፣ መሥዋዕት ተቀባይ፣ መሥዋዕትም ሆኖ ዓለምን ያዳነው፣ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ከራሱም ጋር ታርቆ ያስታረቀን ቡሩክ አምላክ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ነው:: ዳግመኛም መጻሕፍት አምላካውያት "ሰሲሁ ሠዋዒ፣ ወሰሲሁ ተሠዋዒ፣ ወሰሲሁ ተወካፌ ወመሥዋዕት:: ስከ ስተስብእትከ ናቁርብ ሰመሰኮትከ፤ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ሠዋዒ ካህን ነው፤ መሥዋዕቱም እርሱ ራሱ ነው፣ መሥዋዕቱን ተቀባይም እርሱ ነው:: የአንተ የሚሆን የትስብእት ስጦታህን (ገንዘብ) ለጌትነትህ እናቀርባለን" ሲሉ በአንድነት መስክረዋል::

የሃይማኖት ጸሎት በተሰኘውና የክርስትና እምነት የምስክርነት አዋጅ በሚነገርበት የቅዳሴ ሥርዓት ክፍል ሃይማኖታቸው የጸና፣ ምግባራቸው የቀና ሠለስቱ ምዕት (ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት አበው) የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሆነው በጉባኤ ኒቅያ ባረቀቁት ጸሎተ ሃይማኖት ላይ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ድርሻ ሲገልጹ:- "ዘበእንቲአነ ሰሰብእ ወበእንተ ወድኅኒትነ ወረደ እምሰማያት:: ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል:: ኮነ ብእሴ፤ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ስለማዳን ከሰማየ ሰማያት ወረደ፣ ደኩነነ በከመ ትቤለነ ያለችውን ቃሏን ምክንያት አድርጎ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ሰው ሆነ" ብለዋል::[83]

ከላይ ከገለጥነው በተጨማሪ በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያናችን ፍሬ ቅዳሴያት በሙሉ ይልቁንም ደግሞ የእመቤታችን ቅዳሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን የነገረ ማርያም አስተምህሮና ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ በስፋት ይገልጻሉ፣

(83) መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 223:: መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 274:: Messale Engeda (Liqa Kahinat), *Handbook of Ethiopian Orthodox Church*, 23. Mercer, *The Ethiopic Liturgy: Its Sources, Development and Present Form*, 323f.



ያስተምራሉ:: ይህም የሆነበት ምክንያት ጸሎተ ቅዳሴ ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን የፈጣሪዋን የኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ዘወትር የምታዘክርበትና የምታከብርበት፤ በዚህም ምሥጢር አማካይነት ፍሬ መስቀል የሆነውን ሥጋ ወደሙን ለልጆቿ ለምእመናን የምታድልበት ልዩ መንፈሳዊና ሰማያዊ ሥርዓት ነው:: ለምሳሌ ያህል የሊቃውንት ቅዳሴ በሚቀደስበት ጊዜ ሠራዒው ካህን ሥጋ ወደሙን ሲያቀብል "ሥጋሁ ሰአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን ዘነሥአ እምእግዝእትነ ኩልነ ማርያም፤ የሁላችን እመቤት ከሆነችው ከድንግል ማርያም የነሣው የአምላካችንና የፈጣሪያችን የአማኑኤል ሥጋው በእውነት ይህ ነው"[84] በማለት ያውጃል::

ቀደም ብለን እንደገለጥነው መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል አማኑኤል የሚለውን ስም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" ሲል ተርጉሞልናል:: የሰው ልጅ በምክረ ከይሲ ተታልሎ ትእዛዘ እግዚአብሔርን በማፍረሱ ምክንያት የሞት ሞት ተፈርዶበት በመንጸፈ ደይን ወድቆ፣ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቆ ይኖር ነበር:: መጻሕፍት አምላካውያት "ሞታ ሰነፍስ ርሒቅ እምእግዚአብሔር፤ የነፍስ ሞቷ ከእግዚአብሔር አንድነት መለየት ነው"[85] በማለት በአንድነት ይመሰክራሉ:: ይሁን እንጂ በጥንተ ተፈጥሮ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን አንድነት በማጣቱ በፍዳና በመርገም ተይዞ ይኖር የነበረው የሰው ልጅ መድኅን ክርስቶስ በድንግል ማርያም በኩል ባደረገው ሐዲስ ተፈጥሮ ዳግመኛ ከፈጣሪው ጋር የነበረውን አንድነትና ኅብረት ስላገኘ አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆንበትን ድንቅ የተዋሕዶ ምሥጢር ያስረዳናል::

አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የሚለው ትርጓሜ ምሥጢሩም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋን፣ ከነፍሳችን ነፍስን በተዋሕዶ ነሥቶ ሰው ሆነ፣ ባሕርያችንን ከኃጢአት

(84) መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 124::
(85) ፊልክስዩስ፤ መጻሕፍተ መነኮሳት፣ ሁለተኛ መጽሐፍ፤ (አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1982 ዓ.ም.)፣ ገጽ 90-91::

በቀር ፈጽሞ ባሕርዩ አደረገ ማለት ነው። ይህ ታላቅ የድኅነት ጸጋም እስከ ዘላለም ድረስ ጸንቶ የሚኖር ፍሬ ተዋሕዶ ነው። ስለሆነም ወንጌለ ቅዱስ ማቴዎስ በመጀመሪያው ምዕራፍ የተገለጠውንና ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር አንድ የመሆኑን ምሥጢር በማብሠር የሚጀምረውን ዜና ብሥራት በመጨረሻው ምዕራፍም «ወናሁ አነ ሀሎኩ ምስሌክሙ እስከ ኅልቀተ ዓለም፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ፣ ከፍጻሜ ዓለም በኋላም ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28÷20) ተብሎ በተነገረው አምላካዊ ቃል ኪዳን ይፈጽማል። ከላይ እንደገለጥነው ሞት ማለት ከእግዚአብሔር አንድነት መራቅ፣ ከእግዚአብሔር ኅብረት መለየት ማለት ከሆነ በአንጻሩ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር መዋሐድና አንድ መሆን ሕይወት ነው። በዚህም የእግዚአብሔርና የሰው አንድነት ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ የተመሠረተባት ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ምክንያተ ድኅነት፣ መሠረተ ሕይወት መሆኗን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን።

እመቤታችን ድንግል ማርያም በምሥጢረ ሥጋዌ በኲል በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ አስመልክቶ «ማኅተመ አበው» የተሰኘው የቅዱስ ቄርሎስ ቅዳሴ እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

*ከእግዚአብሔር አብ ብቻ መወለዱን እንናገር። ያን ጊዜ እናት አልነበረችውም። የፍጡራን አነዋወር ገና አልታየም ነበርና። ዳግመኛም ምድራዊ አባት ሳይኖረው የአምላክ ልጅ ብቻውን ከዳዊት ልጅ ከድንግል ማርያም ብቻ መወለዱን እንናገር፣ እናውራ።*

*በዘር ለመወለድ አባት ስላልነበረው የሰውነት ሥራ አልጐደለበትም፤ ከብቸኛዋ ሴት ብቻ ፈጽሞ ሰው ሆነ እንጂ።*

*ከአዳም ጐን አጥንት በተፈጠረች ጊዜ እናት ስላልነበረቻት ሔዋን የሴቶች ባሕርይ እንዳልጐደለባት፤ አዳምም የጎኑ አጥንት ስለተነቀለ ከቀደመው የሥጋው ፍጥረት እንዳልጐደለበት፤ እንደዚሁ የአዳምን አባት በሥጋ በወለደችው ጊዜ የማርያም ማኅተመ ድንግልናዋ አልጐደለም ማለት እናትነቷ*



*በድንግልና፣ ድንግልናዋ በእናትነት አልተለወጠም።*

*አዳምን የጎኑ አጥንት በተነቀለ ጊዜ እንዳላሳመመው፤ እንዲሁ የገሊላ ወገን የምትሆን የአምላክን እናት ሕማመ ወሊድ አላገኛትም።*

*እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንታመናለን። ይህ የምንፈትተው ኅብስት ከዕብራውያን ልጅ የነሣው የክርስቶስ ሥጋ እንደሆነ።*

*ዳግመኛም ይህ ጽዋ የእግዚአብሔር በግ ከሚሆን የፈሰሰ ደመ መለኮት እንደሆነ እናምናለን።*(86)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳን ምድራዊ አባት ሳይኖረውና ሳያስፈልገው ከቅድስት ድንግል ማርያም እንበለ ዘር፣ እንበለ ሩካቤ ቢወለድም ቅሉ አንዳችም የትስብእት (የሰውነት) ባሕርይ አልጐደለበትም። ይኸውም ቀዳሚት ሔዋን ምድራዊት እናት ሳያስፈልጋት ከአባታችን ከአዳም ብቻ እንበለ እም (ያለ እናት) ብትገኝም ቅሉ በሔዋን አንዳችም የሰውነት ባሕርይ ካለመጉደሉ ምሥጢር ጋር በምሥጢር ይነጻጸራል፣ ይገናዘባል።(87)

ከላይ የጠቀስነው ይህ የሊቁ ኃይለ ቃል መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በትስብእቱ ከእኛ ጋር የተካከለ፣ በመለኮቱ ደግሞ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ጋር አንድ መሆኑን ያስረዳናል፣ ያስገነዝበናል። መድኃኒታችን ከድንግል ማርያም ሥጋንና ነፍስን በተዋሕዶ መንሣቱ ፍጹም ሰውነቱን ከማጠየቁም በላይ ደቂቀ አዳም ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች ለመሆን መብቃታቸውንም ያረጋግጣል። በአንጻሩ ደግሞ የወልደ እግዚአብሔር ዕሩየ መለኮትነቱ የሰው ልጆችን ድኅነት አማናዊነት የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃና ምስክር ነው። የሥነ መለኮት ሊቃውንት በምሥጢረ ሥጋዌ አማካይነት የተፈጸመውንና በድንግል ማርያም በኲል የተከናወነውን ይህን አምላካዊ የቸርነት ሥራ ቴኦሲስ

---

(86) *መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 386-373።*

(87) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 430። ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 132።*

*[Theosis]*፣ ዲይፊኬሽን [Deification] ይሉታል። የምሥጢረ ድኅነት ቁልፍ የሆነው የዚህ ትምህርት አባት ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ባስተማረበት ድርሳኑ ሲናገር፡- "ወልደ እግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው የሆነው ወልደ እጓለ እመሕያው በጸጋ ውሉደ እግዚአብሔር እንድንሆን ነው" ብሏል። [" The Son of God became the Son of Man so that the son of man might become the son of God; The Son of God became man so as to deify us in Himself. By becoming man He made us sons to the Father."][88]

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከነገረ ድኅነት ጋር በተያያዘ ያላትን ታላቅና ሰፊ ድርሻ አስመልክቶ የእመቤታችን ቅዳሴ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ድረስ የተመሰለውን የተለያየ ኅብ ረ አምሳልና የተነገረውን ኅብረ ትንቢት አምልቶና አስፍቶ በመተንተን እመቤታችን ቤዛዊተ ዓለም፣ መሠረተ ሕይወት መሆኗን በግልጽ ይመሰክራል። ለአብነት ያህል ብንጠቅስ ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ በመኑ ወበአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ። ... ኦ ማዕዶት ዘበኀቤኪ ዓደው እበው ቀደምት እሞት ውስተ ሕይወት። ኦ ምዕራግ እምድር እስከ ሰማይ፤ ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሚ ኩሉ ፍጥረት"[89] ሲል ተናግ ሮአል። ትርጓሜ ምሥጢሩም "ምስጋናንና ክብርን የተመላሽ ድንግል ሆይ በላይ በሰማይ በታች፣ በምድር ባለ ነገር ወይም ማን በተመሰለበት ምሳሌ እንመስልሻለን? ንጽሐ ባሕርይሽና መዓዛ ቅድስናሽ ከዚህ ሁሉ ምሳሌ በላይ ነውና። ዳግመኛም ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና የሆንሽ ድንግል ሆይ ለቃል ርደት፣ ለሥጋ ዕርገት መሰላል የሆንሽ አንቺ ብቻ ነሽ" ማለት ነው።

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የተሰኘው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይህን ኃይለ ቃል ሲተረጉም "ምንትኬ ውእቱ ሰዋስወ ወርቅ ዘእንበለ ዕርገተ ሥጋሁ

[88] Bettenson, *The Early Christian Fathers,* 293. Kelly, *Early Christian Doctrines,* 378-379.

[89] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 227-229።*



ለወልድ እምድብረ ዘይት ውስተ ጽርሐ አርያም" በማለት ዕርገተ ሥጋ በርደተ ቃል የተፈጸመበትን ረቂቅ የተዋሕዶ ምሥጢር አድንቋል። ይኸውም ሊቁ "ዓርገ እግዚእነ ከመ ያስቡ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሐን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቅዱሳን ጻድቃን ዕርገትን ያስረዳና ያጠይቅ ዘንድ በሥጋ ማርያም በሰማይ ደመና፣ በመላእክት ምስጋና፣ በጌትነት፣ በብርሃን፣ በቅዳሴ፣ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ"[90] እንዳለው ነው።

ዳግመኛም ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ከልጅሽ ሰው መሆን አስቀድሞ የነበሩ ቅዱሳን አበው ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሲኦል ወደ ገነት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከኃሣር ወደ ክብር፣ ከመርገም ወደ በረከት፣ ከግራ ቁመት ወደ ቀኝ ቁመት የተሸጋገሩብሽ ምክንያተ ድኂን አንቺ ነሽ በማለት ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ልዩ ሱታፌ ተናግሮላታል። ይህም በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያ ሥላሴ ተ ፈጥሮ ኋላ ግን በምክረ ከይሲ ተታልሎ ዕፀ በለስን በመብላቱ ብልየት (ኃጢአት፣ ጉስቁልና፣ ውርደት) ያገኘው አዳም በሐዲስ ተፈጥሮ የታደሰብሽ ምክንያተ ሕይወት አንቺ ነሽ ማለት ነው።

ከዚህም ጋር ይኸው ሊቅ፡- "አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ደስደደ እምገነት"[91] አዳም ልዑለ ባሕርይ የሚሆን እግዚአብሔርን ያህል ጌታ፣ ገነትን የመሰለች የክብር ቦታ በቀዳሚት ሔዋን ምክንያት አጥቶ፣ በመንጸፈ ደይን ወድቆ፣ በእግረ አጋንንት በተጠቀጠቀ ጊዜ ከፈጣሪው ጋር መታረቂያው፣ ወደ ጥንተ ርስቱ መመለሻ ምክንያቱ፣

[90] አባ ጽጌ ድንግል፣ "ማኅሌተ ጽጌ"፣ ገጽ 162። *መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜ ው፣* ገጽ 242-243። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis of Gasicha] *"መጽሐፈ ምሥጢር"፣ ["The Book of Mystery"]*፤ ገጽ 235። *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 164-165። ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 380፣ 386። *ሚዝሙ ረ ድንግል፣* ገጽ 45-46። Aloys Grillmeier, *Christ in Christian Tradition: From the Apostolic Age to Chalcedan (451),* Rvsd ed. trans. John Bowden (Atlanta: John Knox Press, 1975), 447-448. Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology,* 244.

[91] *ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 71-73። *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 227-229።

ወደ ቀደመ ክብሩ መወጣጫ መሰላሉ፣ መሸጋገሪያ ድልድዩ አንቺ ነሽ» ሲል መስክሮላታል። ይህም ኃይለ ቃል ጌታ «አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ» ያለው ተስፋ ድኅነት በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በኩል መፈጸሙን፣ መታተሙንና መደምደሙን ያስገነዝባል።

በመሆኑም ነገረ ድኅነት [Soteriology] የክርስትና እምነት ጉልላትና የትምህርተ ሃይማኖት ዐቢይ መሠረት ነው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በስፋት ተመዝግቦ እንደምናገኘው በሮማ ምድር የነበሩ ክርስቲያኖች ስደት በታወጀባቸው ጊዜ የካታኮምብ ዋሻ (ግበበ ምድር) የትምህርተ ክርስትናና የሥርዓተ አምልኮ ዋነኛው ማዕከል ነበር። በመሆኑም በወቅቱ የነበሩት ክርስቲያኖች እምነታቸውንና ሥርዓታቸውን በነጻነት ለማካሄድ ባለመቻላቸው ምክንያት እርስ በእርሳቸው የሚተዋወቁበትና የሚገናኙበት ኅቡዕ ምልክት [Hidden Symbol] ይጠቀሙ ነበር።

ይኸውም ለክርስትና እምነታቸው መለያ ሆኖ የሚያገለግል የዓሣ ሥዕል (ቅርጽ) በእጃቸው ላይ ያትሙ ነበር። ይህ ዓይነቱ የጥንት ክርስቲያኖች ጥበብ ከላይ የተመለከትነውንና የክርስትና እምነት አንኳር ምሥጢር የሆነውን ነገረ ድኅነትንና ምሥጢረ ሥጋዌን በአንድነት ይገልጥ ነበር። በግሪኩ ኢኽቱስ [ΙΧΘΥΣ] ዓሣ ማለት ሲሆን እነዚህ አምስት የግሪክኛ ፊደላት በምሕጻረ ቃል [Ιήσους Χρίστου Θέου Υίος Σώτηρ] «ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መድኅን» ["Jesus Christ Son of God, Saviour"] የሚለውን የክርስትና መሠረተ እምነት የሚወክሉና የሚገልጹ ናቸው። ይህም ወደፊት በየምዕራፎቹ ውስጥ የብሉያትን ገጸ ንባብ፣ የሐዲሳትን ትርጓሜና የሊቃውንትን ምሥጢር አብነት አድርገን በስፋት እንደምናየው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ዐቢይ መሠረተ እምነት ነው።



## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በቀዳሚት ሔዋንና በዳግሚት (አዲሲቷ) ሔዋን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም መካከል ያለው አንጻራዊ አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
2. ብሥራተ መልአክ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ምሥጢራዊ ግንኙነት በአጭሩ ይግለጹ።
3. ሐመረ ኖኅ (የኖኅ መርከብ) ከቤዛዊተ ዓለም ከድንግል ማርያም ሁለንተናዊ ሕይወት ጋር ያላትን ምሥጢራዊ ንጽጽር ከነገረ ድኅነት ምሥጢር ጋር በማገናዘብ ያብራሩ።
4. ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በያዕቆብ መሰላል መመሰሏ ከድኅነተ ዓለም ምሥጢር ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
5. የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ ዋና ዓላማ ድኅነተ ዓለም የተፈጸመበትን አምላካዊ የቤዛነት ሥራ በመግለጥ ረገድ ለነገረ ማርያም ትምህርት ያለውን ከፍተኛ አጽተዋጽኦ በአጭሩ ያስረዱ።
6. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ በስንት ይከፈላል? ምን ምን?
7. በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን (በምሥጢረ ሥጋዌ) በኩል የተፈጸመው አምላካዊ የድኅነት ሥራ «ሐዲስ ተፈጥሮ» የተባለበትን ምሥጢር ያብራሩ።
8. ቤዛ ይስሐቅ የሆነው በግ ከመድኅነ ዓለም ከኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ጋር ያለውን አንጻራዊ ትርጓሜ ምሥጢር ይግለጹ።

በመምህር አንዱዓለም ዳግማዊ /B.Th. M.A/
ሚያዝያ/1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

andudag@yahoo.com
andudag.dagmawi@utoronto.ca